ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 220 ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# በሦስተኛው ሩብ ዓመት

## - አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል እህልና ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ሰብዓዊ ድጋፍ ተደርጓል
## - ድጋፍ አቋርጠው የነበሩ ረጂ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራቸው ተመልሰዋል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሦስተኛው ሩብ ዓመት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል እህልና ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ሰብዓዊ ድጋፍ መደረጉን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ። ድጋፍ አቋርጠው የነበሩ ረጂ ተቋማት ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራቸው መመለሳቸውም ተገልጿል።

በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃና ኦፕሬሽን ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ ፍራኦል በቀለ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በሦስተኛው ሩብ ዓመት ማለትም ከጥር እስከ መጋቢት 2016 ዓ.ም ድረስ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዜጎች እርዳታ ተሰጥቷል።

በሦስተኛው ሩብ ዓመት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## በአትክልትና ፍራፍሬ
የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት?

ገጽ 4

## በክልሉ በዘጠኝ
ወራት ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**-ሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት ተመቻችቷል**

ገጽ 4

# በመዲናዋ በከተማ ግብርና ከ108 ሺህ ቶን በላይ ምርት ተገኝቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በመዲናዋ የከተማ ግብርና ከ108 ሺህ ቶን በላይ ምርት መገኘቱን የአዲስ አበባ ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አካሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ሥራ እየተከናወነ ነው፡፡ በዚህም በከተማ ግብርና ከ108 ሺህ ቶን በላይ የአትክልት፣እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ተገኝተዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በከተማ ግብርና መርሐግብር ከእንስሳትና እጸዋት ሀብት ልማት የሚገኘውን የምርት መጠን 104 ሺህ 815 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 108 ሺህ 836 ቶን ምርት ማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም ከእቅድ በላይ ማሳካት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

ምርቱ የተገኘው ከማሳ ሰብል፣ ከግቢና ከጓሮ



በመዲናዋ በከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ታረቀኝ ቡሉልታ

# ውድድሩ የሀገር ውስጥ ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባሻገር የኢንቨስትመንት ዕድልን ለመፍጠር ያለመ ነው

## - የኢትዮጵያ ታምርት ሩጫ ሚያዝያ 13 ይካሄዳል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር የሀገር ውስጥ ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባለፈ የኢንቨስትመንት ዕድልን ለመፍጠር ያለመ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ የ2016 ዓ.ም ኢትዮጵያ ታምርት የሩጫ ውድድር ሚያዚያ 13 ቀን ይካሄዳል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ታረቀኝ ቡሉልታ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ የ2016 ኢትዮጵያ ታምርት የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ሚያዝያ 13 ቀን ለማካሄድ የሚደረገው ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

የሩጫ ውድድሩ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ተመርተው በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ክለቦች የሚጠቀሟቸው የስፖርት ትጥቆችን ከማስተዋወቅ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድልን ለመፍጠር ያለመ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት የምትታወቅ እንደመሆኑ ውድድሩ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ ፣የአምራቾችን ችግር ለመፍታት እንዲሁም ዘርፉ ለሀገር ዕድገት ያለውን አስተዋጽኦ ለማስተዋወቅ እንደሚያግዝ አመልክተዋል።

አብዛኞዎቹ የሩጫ ውድድሩ ተሳታፊዎች ከአምራቹ ዘርፍ የተወጣጡ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ውድድሩ የኢንዱስትሪ ዘርፉን ከስፖርቱ ጋር ከማስተሳሰር በተጨማሪም የገበያ ትስስር የሚፈጠርበትና አምራቾች ልምድ የሚለዋወጡበት እንደሚሆንም ገልጸዋል፡፡

በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ከተመዘገቡ 10 ሺህ ሰዎች ውስጥም ዘጠኝ ሺዎቹ ከአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የተወጣጡ መሆናቸውን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከ22 ክለቦች የተወጣጡ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ፕሮፌሽናል አትሌቶች የሚሳተፉበት የሩጫ ውድድር እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

ውድድሩ ከመስቀል አደባባይ- ሜክሲኮ - ሳርቤት በሚወስደው ጎዳና አድርጎ በጎተራ - መሿለኪያ አድርጎ መዳረሻው መስቀል አደባባይ እንደሚሆን አቶ ታረቀኝ አብራርተዋል፡፡

በሁለቱም ጾታዎች ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ለሚወጡ ተወዳዳሪዎች ከ250 ሺህ እስከ 25 ሺህ ብር የሚደርሱ ሽልማቶች መዘጋጀታቸውን አመልክተው፤ በክለብ ደረጃ ለሚወዳደሩ ደግሞ በሁለቱም ጾታዎች ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ለሚወጡ ከአንድ መቶ ሺህ እስከ 50 ሺህ ብር ሽልማት ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት ሩጫ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በጋራ የሚያዘጋጁት ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ የሩጫ ውድድር መስፈርቶችን ባሟላ ሁኔታ እንደሚካሄድ ተጠቁሟል።

# ሥልጠናው ሥራችንን በብቃት ለመፈጸም ስንቅ ያገኘንበት ነው

## - ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ ለሰባት ተቋማት ሲሰጥ የቆየው ሥልጠና ተጠናቀቀ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሥልጠና ማዕከል ያገኘነው ሥልጠና ሥራችንን በብቃት ለመፈጸም ትልቅ ስንቅ ያገኘንበት ነው ሲሉ ሥልጠናውን የተከታተሉ ሠልጣኞች ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሥልጠና ማዕከሉ ከመጋቢት 26 እስከ ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በፎቶ ጋዜጠኝነት፣ በግራፊክስ አርት እና በብራንዲንግ ንድፈ ሃሳብና ቴክኒክ የሥልጠና ዘርፎች ለሰባት ተቋማት ባለሙያዎች ሲሰጥ የቆየው ሥልጠና ትናንት ተጠናቋል።

የፎቶ ጋዜጠኝነት ሠልጣኝ እና ከአዲስ አበባ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሠራተኛ አቶ ተስፋዬ ዘውዱ እንደገለጹት፤ በተለያዩ ጊዜያት የፎቶ ጋዜጠኝነትን ንድፈ ሃሳብ የመማር እድሉ ገጥሞኛል። ነገር ግን ተግባር ተኮር ሥልጠና ያገኘሁት በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ነው።

“ይህ ሥልጠና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሥራ የሚያግዝ እውቀት እንድጨብጥ አድርጎኛል” ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ያገኙት ሥልጠና ለሥራቸው ትልቅ ግብዓት ያገኙበት እንደሆነ ገልጸዋል።

ኢፕድ ለረጅም ዓመታት ያካበተውን ልምድ ለሌሎች ተቋማት ለማካፈል የሥልጠና ማዕከል መክፈቱ የሚበረታታ ነው ብለዋል።

የግራፊክስ አርት ሠልጣኝ እና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ሠራተኛ አቶ ሙላቱ ሙጬ በበኩላቸው፤ በተሰጣቸው ሥልጠና ትልቅ እውቀት እንዳገኙበት ገልጸው፤ በቀጣይ ያገኙትን እውቀት በመደበኛ ሥራቸው እንደሚጠቀሙበት ተናግረዋል።

በአሠልጣኞቹ ብቃት መደሰታቸውን የገለጹት አቶ ሙላቱ፤ የሥልጠናው ጊዜ ቢራዘም ለሥራቸው እንደሚያግዛቸው እና በተለያዩ የሥልጠና ዓይነቶች በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል መውሰድ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድም ተክሉ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ኢፕድ በየዘመኑ እያካበተ የመጣውን ልምድ ለሌሎች ተቋማት ማካፈል አለበት በሚል በአሥር ዓመት ስትራቴጂክ እቅዱ ውስጥ አካትቶ እየሠራ ነው።

ለፌዴራልና ለክልል አመራሮችና ባለሙያዎች ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት የሥልጠና ማዕከል አቋቁሞ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ወንድም፤ በሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ተቋማት ውጤታማ እንዲሆኑ የተለያዩ የሥልጠና ዓይነቶችን አዘጋጅቶ እያሠለጠነ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በተለይም የተቋማት ውስንነቶችን በማረም ወደ ሥራ ከማስገባት አንጻር ውስንነቶች አሉ ያሉት አቶ ወንድም፤ ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ የሚሰጠው ሥልጠና በተቋማት የሚስተዋሉ ውስንነቶችን ለማረም ይረዳል። ይህም የተቋምን ገጽታ በስፋት በማስተዋወቅ እና የሚሰነዘሩ ትችቶች እንዲታረሙ በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ሠልጣኞች ባሉበት የሥራ ቦታ የተሰጣቸውን ሥልጠና ውጤታማ እንዲያደርጉ የሚያስችል ድጋፍ እንደሚያደርግም ገልጸው፤ ኢፕድ በሥልጠና ማዕከል በተያዘው በጀት ዓመት ማለትም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ60 በላይ የሚሆኑ ተቋማት ሙያተኞችን ማሠልጠኑን ተናግረዋል።

ሥልጠናቸውን ያጠናቀቁት ሠልጣኞች የሥልጠና ማዕከሉ 25ኛ ዙር ሠልጣኞች ሲሆኑ፤ ከዚህ በፊት የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል በ24 ዙሮች የፌዴራልና የክልል ተቋማትን ሠራተኞችና አመራሮችን በተለያዩ የሥልጠና ፕሮግራሞች አሠልጥኗል።

ከዳግማዊ ምኒልክ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት፣ ከፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት፣ ከ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን እና ከግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የተውጣጡ 25 ሠልጣኞች ሥልጠናውን ተከታትለዋል።

# ስምምነቱ ለሀገር ጠቃሚና ጥራት ያለው መረጃ ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- ስምምነቱ ለሀገር ጠቃሚና ጥራት ያለው መረጃ ተደራሽ ለማድረግ እንደሚረዳ ገልጿል፡፡ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የላሳክ ( LASAC) land Satellite remote Sensing Application Center መረጃን መጠቀም የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮጵያ ስታትስቲክ አገልግሎት ጋር በትናንትናው እለት ተፈራረመ።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ስታትስቲክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር በከር ሻሌ እንደገለጹት፤ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን መረጃ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ መረጃ ለውሳኔ ሰጪነት ፣ የፖሊሲ፣ ለምርምር እንዲሁም ሁሉም ዘርፎች መሰረት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ስምምነቱ ለሀገር ጠቃሚና ጥራት ያለው መረጃ ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ዘመን የመረጃዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉና ወደ ግዙፍ መረጃ ምንጭ ያደሉ ሆነዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የኢትዮጵያ ስታትስቲክ አገልግሎትም ይህን በመረዳት በተለይም ጥራት ያለው ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ የተለያዩ አማራጮችን ሲቃኝ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

አገልግሎቱ ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን በተለይም ለሀገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርናው ዘርፍ መረጃ ለመሰብሰብ በድሮን ጭምር የታገዘ ሥራ ማከናወኑን ገልጸዋል፡፡

በዋና ዳይሬክተሩ፤ የተደረገው ስምምነትም ፈጣን፣ታማኝ ፣ወቅታዊ እንዲሁም ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ጥራት ያለው መረጃ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ ለተሻለች ኢትዮጵያ የተሻለ መረጃ ማቅረብ የሚቻልበትን አቅም የሚገነባበት እንደሚሆንም ተናግረዋል፡፡

የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ እንደገለጹት፤ ላሳክ (LASAC) ሀገር አቀፍ ሽፋን ያለው የሁለት ሜትር ሪዞሉሺን መረጃ መሰብሰብ የሚችል ማዕከል ነው፡፡ ስምምነቱም ከዚህ ማዕከል የሚመጡ መረጃዎችን ወደ ተቋማት በነጻ በመላክ ጥቅም ላይ እንዲያውሉት የሚያደርግ ነው፡፡

ይህን መረጃ በገንዘብ ሲተመን ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያወጣል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ተቋሙ ይህን መረጃ ከኢንስቲትዩቱ ወስዶ ለሦስተኛ ወገን መሸጥም ሆነ ማስተላለፍ አይችልም ብለዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ቤተልሄም ንጉሴ በበኩላቸው ፤ኢንስቲትዩቱ በ2015 ዓ.ም የላሳክ መረጃን ለአምስት ዓመት በነፃ ለማግኘት ከቻይና መንግሥት የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ጋር ስምምነት አድርጓል።

ከስምምነቱ በኋላም የኢትዮጵያን ሙሉ የቆዳ ስፋት የሚሸፍን መረጃ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

የተገኙ መረጃዎችን በመረጃ ቋት በማከማቸት እንዲሁም መረጃዎቹን በኢንስቲትዩቱ ባሉ ባለሙያዎች የምርምር እና የፕሮጀክት ሥራ ላይ ሲውል መቆየቱን ገልጸው፤ ይህም በቂ ባለመሆኑ የፌዴራልና የክልል ተቋማት የላሳክ መረጃዎችን በኢንስቲትዩቱ በኩል ወስደው ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ይህ ስምምነት አስፈልጓል ሲሉ ተናግረዋል።


ተቋማት የሚወስዱትን መረጃ ለጥናትና ምርምር ማዋል ይጠበቅባቸዋል ያሉት ኢንጂነር ቤተልሄም፤ የተሠሩ ሥራዎችንም በየስድስት ወሩ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ያለማውን NSDI (national Spatial data Infrastructure )የተሰኘ መተግበሪያ ይፋ አድርጓል፡፡ መተግበሪያው ተቋማት የጂኦስፓሻል መረጃዎችን ባሉበት ሆነው በቀላል መንገድ እንዲያገኙ የሚያግዝ መሆኑም በመድረኩ ተገልጿል።

# የመዲናዋ የሰላም ማስከበር ተግባር የልማት ሥራዎች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ እገዛ እያደረገ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**


ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ


ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ እየተሠራ ያለው ሰላም የማስከበበር ተግባራት የልማት ሥራዎች በተያዘላቸው ቀነ ገደብ እንዲጠናቀቁ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው ሲል የአዲስ አበባ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮና የአዲስ አበባ ደንብ የማስከበር ባለስልጣን የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር እቅድ አፈጻጸም ላይ ትናንት በጋራ ውይይት አካሂደዋል።

የግምገማ ውይይቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ እየተሠራ ያለው ሰላም የማስከበር ተግባራት በከተማዋ እየተሠሩ ያሉ የተለያዩ የልማት ሥራዎች በተያዘላቸው ቀነ ገደብ እንዲጠናቀቁና ተቋማት የተፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ነው፡፡

የመዲናዋን ማህብረሰብ የሰላም ባለቤት ለማድረግ እየተሠራ ያለው ሰላም የማስከበር ሥራ ትልቅ ውጤት እያስገኘ ነው ያሉት ወይዘሮ ሊዲያ፤ እየተሠሩ ያሉ የልማት ሥራዎችም በቀነ ገደባቸው እንዲጠናቀቁ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል ብለዋል፡፡

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በመዲናዋ ትላልቅ ኦፕሬሽን በመሥራት ደረቅ ወንጀሎችን የመከላከልና የፅፈኛ ኃይሎች እኩይ ተግባር የማክሸፍ ሥራ ተሠርቷል ያሉት ወይዘሮ ሊዲያ፤ የደረቅ ወንጀልንና የሽብር እንቅስቃሴን አስቀድሞ የመከላከል ሥራ የመዲናዋ እድገት እንዲፋጠን የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ፅንፈኛና ፀረ ሰላም ኃይሎች ከተማዋን የብጥብጥ ማዕከል ለማድረግ የሚያደርጉትን እኩይ ተግባርንና ወንጀልን አስቀድሞ የማክሸፍና አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሥራ እየተሠራ ነው፤ይህም የከተማዋ ሰላም እንዲሻሻል አድርጎታል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በመዲናዋ ሕገ ወጥ የገንዘብና የጦር መሳሪያን ዝውውር ወንጀል የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ እየተሠራ ባለው ሥራም ወንጀሎችን መከላከል ተችሏል ብለዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሊዲያ ገለጻ፤ በሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ እየተወሰደ ያለው ሕጋዊ እርምጃና አስተዳደራዊ ቅጣት የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት እየተሠራ ያለው ሥራ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

በመዲናዋ ሰላምን ለማስከበር እየተሠሩ የሚገኙ ውጤታማ ተግባራትም ልማቶች በተያዘላቸው ቀነ ገደብ እንዲጠናቀቁ ያደርጋል፡፡ ይህ ተግባርም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አመልክተዋል፡፡


የአዲስ አበባ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በበኩላቸው፤ በመዲናዋ ሕገ ውጥ ንግድን ለመከላከል እየተሠራ ያለው ሥራ ወንጀሉን ከመከላከል በተጨማሪ ከተማዋ ውበቷ እንዲጠበቅ እያደረገ ነው፡፡

በመዲናዋ ሕገ ወጥ የጎዳና ንግድን ለመከላከል እየተራ ያለው ሥራ ነዋሪውን በነፃነት እግረኛ መንገዱን እንዲጠቀም አስችሏል ብለዋል፡፡

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የጎዳና ንግድንና ሕገወጥ የመሬት ወረራ ወንጀልን የመከላከልና ሕግን የማስከበር ሥራ እየሠራ ነው፡፡ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሻለቃ ዘሪሁን ጠቁመዋል፡፡

# የኢትዮጵያን የ100 ዓመታት የግብርና ታሪክ የሚዳስስ መጽሐፍ ሊመረቅ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**




አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የ100 ዓመታት የግብርና ታሪክ ውስጥ በግብርናው ዘርፍ የተወሰዱ ርምጃዎችን እና የተገኙ ውጤቶችን የሚዳስስ መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል።

“ኢትዮጵያ ከግብርናና ከምግብ ቀውስ ነፃ ስለመውጣት፤ ተቋማዊ ዝግመተ - ለውጥና የግብርናና ገጠር ልማት ሽግግር ጎዳና” በሚል ርዕስ የተዘጋጀው መጽሐፍ በግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ አማካሪ እና ተመራማሪ ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር) የተዘጋጀ ሲሆን፤ አሳታሚው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ነው።

የመጽሐፉ አዘጋጅ ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ መጽሐፉ የግብርናው ዘርፍ አፈጻጸም ላይ ትኩረት ያደረጉ 12 ምዕራፎች አካቶ ይዟል። በዚህም ኢትዮጵያ በዓለም የእርሻ ታሪክ ውስጥ የነበራትን ሚና የሚዳስሱ ሦስት ምዕራፎች ተካተዋል።

መጽሐፉ በኢትዮጵያ የ100 ዓመታት የግብርና ታሪክ ውስጥ የተወሰዱ ርምጃዎችን እና የተገኙ ውጤቶችን ይዳስሳል ያሉት ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር)፤በ100 ዓመታት ጊዜ ውስጥ መንግሥታት እና ተቋማት በግብርናው ዘርፍ የተወሰዱ ርምጃዎች የኢትዮጵያን የግብርና ሥርዓት ምን ያህል ማሻሻል ችለዋል የሚለው በመጽሐፉ ውስጥ በዝርዝር ተዳስሷል ብለዋል።

መጽሐፉ የግብርናውን ዘርፍ ከጊዜ፣ ከመዋቅር፣ ከተቋም እና ከውጤት አንፃር በስፋት ይዳስሳል ያሉት ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር)፤ መጽሐፉ እነዚህን ጉዳዮች በአርሶ አደሩ፣ በአርብቶ አደሩ እና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያመጡት ለውጥ እንደሚያስረዳ ተናግረዋል።

መጽሐፉ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የታተመ ነው። በአማርኛ ቋንቋ የታተመው 347 ገጾች ያሉት ሲሆን በእንግሊዘኛ ቋንቋ የታተመው ደግሞ 435 ገጾች ያሉት መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር) ገለጻ፤ በዓለም የግብርና ታሪክ ኢትዮጵያ የረቀቀ ሞፈርና ቀንበር የነበራት እንዲሁም የጤፍ፣ የገብስ እና የበርካታ እህሎች መገኛ ሆና ተገልጻለች። በመጽሐፉም ኢትዮጵያ በዓለም የእርሻ ታሪክ ውስጥ ግንባር ቀደም መሆኗን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች ተጠቅሷል።

በዚህም በኢትዮጵያ የግብርና እድገት ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶች እና የተወሰዱ የመፍትሔ ሃሳቦች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የነበራቸው ውጤት በስፋት ተዳሷል ያሉት ጌታቸው ድሪባ (ዶ/ር)፤ በቀጣይ በግብርናው ዘርፍ ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባ እና በዘርፉ ለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ምን አይነት የመፍትሔ ሃሳቦች ማዘጋጀት እንደሚገባ መጽሐፉ ይጠቁማል ብለዋል።

**የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን**
**Ethiopian Maritime Authority**

# ባለስልጣኑ

## የተሰጠውን የኦዲት ግኝት ማስተካከያ እንዲተገብር ተጠየቀ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የተሰጠውን የኦዲት ግኝት ማስተካከያ እንዲተገብር ተጠየቀ።

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የማሪታይም ባለሥልጣን የ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ውይይት በተካሄደበት ወቅት የፌዴራል ምክትል ዋና ኦዲተር አቶ አበራ ታደሰ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ ዋና ኦዲተር ማስተካከያ እንዲያደርግ ባሳወቀው መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎች ቢኖሩም አሁንም ያልተስተካከሉ ግኝቶች አሉ።

ከእነዚህም መካከል በተለያዩ ጊዜያት ዓመታዊ የእቅድ አፈጻጸምና ግምገማዎች ሲካሄዱ ሠራተኞች ስለመገኘታቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ አለመፈረማቸው እንዲሁም ከመ/ቤቱ ውጪ የመጡ መገጣጠሚያ ደብዳቤ ሳያቀርቡ 261 ሺ 429 ብር አላግባብ አበል ተከፍሏል። አስራ ስድስት ለሚሆኑ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ለሥራ ጉዳይ በሄዱባቸው የተለያዩ ቦታዎች መከፈል ከሚገባው የአበል ተመን በላይ 5 ሺ 235 ብር መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡

በተመሳሳይ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ የሚከናወኑ ሥራዎችን ለኮሚሽኑ በማሳወቅ ክፍያ መፈጸም ሲገባቸው ፈቃድ ሳያገኝ ከመመሪያ ውጪ 11 ሺ 291ብር ከ50 ሳንቲም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈጽሟል። ሠራተኞች አዲስ አበባ ለሰለጠኑባቸው ቀናት በሚል በቀን አንድ መቶ ብር በማሰብ 81 ሺ 400 ብር ክፍያ ተፈፅሟል። በተጨማሪ ከግዢ፤ ከተሰብሳቢና ከተከፋይ ሂሳብ እንዲሁም ከበጀት አፈጻጸምና የንብረት አያያዝ ጋር ክፍተቶች ተገኝተዋል። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች በአጭር ጊዜ ተቋሙ ሊያስተካክል እንደሚገባ አሳስበዋል።

በገንዘብ ሚኒስቴር ኢንስፔክሽን መምሪያ አቶ መኮንን ጌታሁን በበኩላቸው የ2014 ዓ.ም የዋና ኦዲተር ምላሽ ከተሰጠ በኋላ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል። የእርምት እርምጃ የተወሰዳባቸው፤ ተመላሽ የተደረጉ ገንዘቦችንና ለመመለስ በቀጠሮ ያሉትን የጊዜ ገደቡን እንዲያስቀምጡም አድርጓል።

በቀጣይ እርምጃ የሚወሰድባቸውም ላይ እንዴትና ምን አይነት እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚቻል በጋራ ውይይት ተደርጓል። ግዢን በተመለከተም ተጠያቂነትን ለማስፈን የሄዱበትን ርቀትና በኦዲት የተገኙ ስህተቶች አለመደገማቸውን የማረጋገጥ ሥራ ተከናውኖ ለተቋሙና ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ ተሰጥቷል ብለዋል።

በዚህም መሠረት እስከ ሚያዝያ ሰላሳ ድረስ እርምጃ ባልተወሰደባቸው ላይ እርምጃ ወስደው እንዲያቀርቡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል። ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን ከሚያዝያ ሰላሳ በኋላ ገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ወደ እርምጃ የሚገባ ይሆናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዱልበር ሽምሱ የኦዲት ክፍቱን በመቀበል በሰጡት ምላሽ በናሙና ኦዲት የተገኙ ግኝቶች የምናስተካክላቸውና አስተማሪ ናቸው ብለዋል።

ግኝቶቹ በገንዘብ ደረጃ ዝቅተኛ ቢሆኑም የክትትልና የቁጥጥር መርሀ ግብር በማዘጋጀት አሠራራችን ሕግና ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ እንዲሆን የምናደርግ ይሆናል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እስካሁንም የዋና ኦዲተር ግብረ መልስ ከተሰጠን ጀምሮ በርካታ ማስተካከያዎችን ስናደርግ ቆይተናል ብለዋል።

አንዳንዶቹ ነገሮች በሕግ አግባብ የማይፈቀዱ ቢሆንም ስህተት ሆነው ሳይሆን በሁኔታዎች አስገዳጅነት የተከናወኑ መሆናቸውንም ለቋሚ ኮሚቴውና ለዋና ኦዲተር አስረድተናል። ይህም ሆኖ በሚቀጥሉት ሃያ ቀናት የሚጠበቅብንን በማስተካከል ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት የምናሳውቅ ይሆናል ብለዋል።

ዜና

## በአትክልትና ፍራፍሬ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት?

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ኢትዮጵያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ አምርቶ የመጠቀም ሰፊ እድሎች እንዳሏት ይነገራል፡፡ ሀገሪቱ ካላት ለምለም መሬት ሰፊ የውሃ ሃብትና በርካታ ወጣት ኃይል አኳያ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ በተጨማሪ ለውጭ ምንዛሪና ለሥራ እድል ፈጠራ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን የዘርፉ ሙሁራን ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ዘርፍ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዳልተቻለም ይነገራል፡፡ በመሆኑም አሁን በሀገሪቱ ለሚስተዋለው የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበትና ሥራ አጥነት ለመቀልበስም ሆነ በዘርፉ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በዘርፉ ያለውን እድል ወደ ውጤት መቀየር የግድ መሆኑን ሙሁራኑ ያክላሉ፡፡

ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የባዮ-ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር ባያብል አጥናፉ(ዶ/ር)፤ዘርፉ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ያለው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም የምርትና የድህረ ምርት ሂደቱ በምርምር የተደገፈ ባለመሆኑ ህብረተሰቡ ከዚህ ዘርፍ ባለው አቅም ልክ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ምርቱ በሚያጋጥመው ብልሽት ኪሳራ ከማስከተሉም በላይ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆን እንዳደረገው ያብራራሉ፡፡

ዘርፉ ከ30 እስከ 40 በመቶ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው የሚሉት ዶክተር ባያብል፤ኢትዮጵያ የማምረት አቅሟ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉ ሀገራት መካከል እንደሆነች ይገልጻሉ፡፡

በተለይ የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ የምርት የጥራት ደረጃ ማረጋገጥና የከተማ ግብርናው የምግብ ዋስትናን እንዲያረጋግጥ እንዲሁም ተረፈ ምርቱ ብክለት እንዳያስከትል በጠንካራ ፖሊሲ መመራት እንዳለበትም ምክረ-ሃሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡

ኢትዮጵያዊያን በሳምንት አንዴ ብቻ አትክልትና ፍራፍሬ እንደሚመገቡ ጥናቶች ያሳያሉ የሚሉት ዶክተር ባያብል፤ምርትና ድህረ ምርቱ በምርምር ካልተደገፈ ውጤቱን ማሰብ እንጂ ማግኘት አይቻልም ይላሉ፡፡ ሳይንሳዊ መንገድ በመከተል ምርት ማምረት ከተቻቸ የሀገሪቱ አጠቃላይ ገቢን ከማሳደግ አኳያ ሰፊ እድል እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ለአብነትም ኬንያ ለዘርፉ ትኩረት በመስጠቷ ከአጠቃላይ ገቢዋ 40 በመቶ ከአትክልትና ፍራፍሬ የሚገኝ ነው፡፡

አትክልትና ፍራፍሬ በንጥረ ነገር ይዘታቸው የምግብ ዋስትና በቀላሉ ለማረጋገጥ ይችላሉ የሚሉት ደግሞ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ የእጽዋት ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ዘነበ መኮንን(ዶ/ር) ናቸው፡፡

በዘርፉ የተለያዩ ምርምሮች ቢደረጉም ለባለሙያው የሚከፈለው ክፍያ ዝቅተኛና የባለሙያው ተነሳሽነት አለማደግ ውጤት አልባ አድርጎታል ባይ ናቸው፡፡

የሰብል ጥበቃ፣ የተሻለ ዝርያና ዘመናዊ ማሽኖች ከማቅረብ አኳያ ውስንነቶች ቢኖሩም አሁን ላይ የሚታዩ እንቅስቃሴዎች አበረታች መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ "ምርምሮች በየጊዜው ይደረጋሉ፤ ነገር ግን ወደ ተግባር መቀየር ላይ ውስንነቶች አሉ" የሚሉት ዶክተር ዘነበ፤ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት ረገድ የድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ የምርት ጥራት ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ባይ ናቸው፡፡ የተመረቱ ምርቶችን ሳይበላሹ የሚያቆዩ መጋዘኖች እንዲሁም የክህሎት ሥልጠና በየጊዜው መስጠት እንደሚያስፈልግም ዶክተር ዘነበ ይገልጻሉ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሆልቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብደላ ነጋሽ በበኩላቸው ዘርፉ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ዘርፉ ከአግሮ ኢንደስትሪ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ግብዓት የሚሆን በመሆኑ የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩም ተጨማሪ ስራዎች መስራት እንደሚያስፈልግ ነው የሚናገሩት፡፡

ለስራ እድል ፈጠራ ትልቅ አቅም ያለው ዘርፍ ነው በትንሽ መሬት ላይ ብዙ ምርትና በርካታ የሰው ኃይል ማሳተፍ የሚችል ነው የሚሉት መሪ ሥራ አስጻሚው፤ በጥሬው ወደ ውጭ ከመላክ እሴት ጨምሮ መላክ ቢቻል ከውጭ ምንዛሪ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ የሚችል ነው፡፡ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆንም ለውጭ ገበያው የሚቀርበው ምርት ዝርያ የመምረጥ፣ የጥራት ደረጃ ማውጣትና በሀገር ውስጥ ዘር አባዦች እንዲባዙ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሆኑ ያብራራሉ፡፡

ለውጭ ገበያ የሚላኩ ምርቶች የጥራት ችግር በሁሉም ላይ አይደለም የሚሉት አቶ አብደላ፤ የኢትዮጵያ የአቮካዶ ምርት በዓለም ገበያ ተፈላጊ ነው፡፡ ከድህረ ምርት ጋር በተያያዘ የሚከሰተው ብክነትና የሚስከትለውን ጉዳት ለመቀነስም እስትራቴጂዎች ተነድፈው ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ለይ ስለመሆናቸውንም ያስረዳሉ፡፡

# በክልሉ በዘጠኝ ወራት

## ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**- ሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት ተመቻችቷል**

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የኦሮሚያ ክልል ሥራ ዕድል ፈጠራ እና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ፡፡ ሥራ ዕድል ለተፈጠራቸው ዜጎችም ሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት መመቻቸቱ ተገልጿል፡፡

በክልሉ የሥራ ዕድል ፈጠራ እና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኤባ ገርባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በተለይም በግብርናው ዘርፍ በተሠራ ሰፊ ሥራ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በከተማ እንዲሁም በገጠር በተለያዩ የሥራ መስኮች ለሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

አቶ ኤባ፤ 136 ሺህ የሚሆኑ አዲስ ኢንተርፕራይዞች መፈጠራቸውን ግልጸው፤ ከዚህ ውስጥም 55 በመቶ የሚሆኑት በግብርናው ዘርፍ በሰብል እና በእንስሳት እርባታ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በዘንድሮው ዓመት በተለይ በግብርናው ዘርፍ የተሠራው ሥራ ከፍተኛ ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በሁሉም ከተሞች በክላስተር በማቀናጀት የዶሮ እርባታ፣ የከብት እርባታ እንዲሁም ወተት ምርት ላይ ሰፊ ሥራ ተከናውኗል ብለዋል፡፡

መንግሥት ከኅብረተሰቡ ጋር በመሆን ለወጣቶች የመስሪያና መሸጫ ቦታን የማመቻቸት ሥራዎችን በስፋት ማከናወኑን የገለጹት አቶ ኤባ፤ በዚህም ከአምስት ሺህ የመሥሪያ ቦታዎች (ሼዶች) በላይ በክላስተር ወደ ኢንተርፕራይዞች የተላለፈ ሲሆን፤ በተጨማሪም ሦስት ትናንሽ የመሸጫ ሼዶች ተገንብተው መተላለፋቸውን ገልጸዋል፡፡

በገጠር በተከናወነ ሥራ ወጣቶችን ሰፊ ቦታዎች ላይ በማስፈርና በማህበር በማደራጀት የሻይ ቅጠል ፣ ፍራፍሬ



አቶ ኤባ ገርባ

እንዲሁም የሩዝ ምርት ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ውጤታማ ማድረግ ማስቻሉን አመልክተው፤ ይህም በተለይ በጅማ ዞን አመርቂ ውጤት ማሳየቱን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ወጣቶች ወደ ሥራ ሲገቡ የገንዘብ እጥረት ችግር እንዳይኖርባቸው በዘጠኝ ወር ውስጥ ሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር የብድር አቅርቦት ማመቻቸት ተችሏል ፡፡ሆኖም ከባንኮች የሚገኘው የብድር መጠን በቂ አለመሆንና በተለይም ከሲንቄ ባንክ መገኘት የነበረበት ብድር ከቢሮክራሲ ጋር ተያይዞ ባለመገኘቱ ሥራው ላይ ትልቅ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡

ከሲንቄ ባንክ የተገኘው ብድር 800 ሚሊዮን ብር ብቻ መሆኑን ያነሱት አቶ ኤባ፤ቢሮው ይህን በመረዳት በተለያየ መንገድ የወጣቱ ብድር የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቷል ብለዋል፡፡

በክልሉ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ተደርጎ ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ቢቻልም አሁንም በክልሉ ሥራ አጥ የሆነ ወጣት ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ኤባ፤ በቀጣይም አካባቢውን በመቃኘትና ያለውን ሀብት አሟጦ በመጠቀም የሥራ አጥነትን ችግር ለማቃለል ሀገሪቱን ለማበልጸግ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# በመዲናዋ በከተማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አትክልት፣ ከእንስሳት ዕርባታ፣ ከዶሮ እርባታና ከንብ ማነብ እንደሚገኙበት ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፣ በዘርፉ የሚገኘውን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የተሻሻለ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓት፣ የእንስሳትና የእጸዋት ዝርያዎችን የማሰራጨት እና ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በከተማ ግብርና በእጽዋት ሀብት ልማት ለሚሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች ከአንድ ሺህ 900 ኪሎ ግራም በላይ የእንጉዳይ ዘር፣ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኝ መሰራጨቱን ተናግረዋል፡፡

ስምንት ሺህ 115 እንስሳትን ማዳቀል፣ ለ432 ሺህ 984 እንስሳት ሕክምና መስጠት እና 53 ሺህ 506 የተሻሻሉ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት መቻሉን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በከተማ ግብርና ከ638 ሺህ በላይ የማህበረሰብ ክፍሎችና ከሁለት ሺህ 200 በላይ ተቋማት እየተሳተፉ ነው ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ በቀጣይ የከተማ ግብርናን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል የተሳታፊ ቁጥር የመጨመር እና የከተማ ግብርናን የማዘመን ሥራ እንደሚሠራ አስታውቀዋል፡፡

የነበሩ ድክመቶችን በመለየት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ድክመቶችን ማረም፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን መጨመር፣ የድጋፍና ክትትል ሥራውን እስከታችኛው ደረጃ ማውረድ፣ ልምድና ተሞክሮዎችን መለዋወጥ የትኩረት አቅጣጫ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በከተማ ግብርና መርሀ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በጓሮ አትክልትና በእንስሳት እርባታ የምግብ ፍጆታቸውን እንዲሸፍኑ ከማስቻሉም ባለፈ የከተማው ነዋሪዎችም አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ እንቁላል፣ ወተት እና ሌሎች ምርቶችን በተመጣጠነ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ በማድረግ ገበያውን ለማረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

# በሦስተኛው ሩብ ዓመት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በጥር ወር ብቻ 666 ሺህ ኩንታል እህልና 446 ሚሊዮን ብር መሰራጨቱን አስታውቀዋል። በተመሳሳይ በየካቲት ወር ላይ ደግሞ 587 ሺህ ኩንታል እህልና 802 ሚሊዮን ጥሬ ገንዘብ ለተረጂዎች መድረሱን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም በመጋቢት ወር 385 ሺህ ኩንታል እህልና 891 ሚሊዮን ብር ማሰራጨት እንደተቻለ ተናግረዋል።

በአጠቃላይ በሦስተኛው ሩብ ዓመት በአማካይ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ወገኖች አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል እህል እና ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል ነው ያሉት።

ድጋፉ በመንግሥትና ረጂ ተቋማት አማካኝነት እንደተደረገ ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት የአጋር ድርጅቶች ድጋፍ አሰጣጥና ቁርጠኝነት አበረታች መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህም በመንግሥትና አጋር ድርጅቶች አማካኝነት በበጀት ዓመቱ ሦስተኛው ሩብ ዓመት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል እህልና ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ሰብዓዊ ድጋፍ ተደርጓል ያሉት ፍራኦል (ዶ/ር)፤ ከዓለም ባንክ የተገኘን ድጋፍ ጨምሮ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ድጋፉን አግኝተዋል ሲሉ ገልጸዋል።

አጋር ድርጅቶች ከሰብዓዊ እርዳታ ጋር ተያይዞ ለተወሰነ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ድጋፍ አቋርጠው ነበር። በተደረጉ ውይይቶችም መፍትሄ በማግኘት ድጋፍ ወደ ማድረጉ መመለሳቸውን አስታውቀዋል።

ዶክተር ፍራኦል እንዳሉት፤ የችግሩ መንስኤ ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ፤ ከተረጂ ልየታና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ያለው ቅሬታ ላይ ግልጽነት እንዲኖረው በማድረግ ድርጅቶቹ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ተመልሰዋል። የዓለም ምግብ ፕሮግራምን ጨምሮ ድጋፍ ያቋረጡ አጋር አካላት የተግባር ክንዋኔ በሚያደርጉባቸው አካባቢዎች ስራቸውን ሙሉ ለሙሉ ጀምረዋል። ሽፋናቸውንም እያሰፉ ይገኛሉ። ጥሬ ገንዘብና ምግብ ነክ ድጋፎችን ለተረጂዎች እያደረሱ ነው።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ከድርቅ ጋር ተያይዞ የምግብ ክፍተት እንዳለ በመጥቀስ፤ በዚሁ መሠረት በአራተኛው ሩብ ዓመትም ጥናቶችን መነሻ በማድረግ መንግሥት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ክፍተቱን የመሙላት ሥራ ይሠራል ብለዋል። በሰሜኑ ጦርነት ሳቢያ እንዲሁም ከግጭት ጋር ተያይዞም ተፈናቃይ ወገኖች ለምግብ እጦት እንዳይዳረጉ መንግሥት በሚችለው አቅም ልየታ አድርጎ ድጋፉን እንደሚቀጥል ነው የገለጹት።

ግጭት ባለባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ምግብ ነክ ድጋፍ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙም መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ለዜጎች እርዳታ እየሰጠ እንዳለም ጠቅሰዋል።

እንደ አማራጭ ከተወሰዱ መፍትሔዎች ውስጥም አጋር ድርጅቶችን በመጠቀም ድጋፍ ማድረግ እንደተቻለ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ኮማንድ ፖስት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ሰብዓዊ ድጋፉ በፀጥታ ኃይሉ ታጅቦ ለማህበረሰቡ እንዲደርስ ተደርጓል ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሁፍ፤ ኢትዮጵያ፣ ብሪታኒያና የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ (ኦቻ) ባዘጋጁት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ኮንፍረንስ ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ለኢትዮጵያ ሰብአዊ እርዳታ የሚውል ከ630 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገንዘብ ተሰብስቧል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ቀዳሚ ትኩረት የዜጎችን ኑሮ ማሻሻል፣ የአደጋ ስጋት ቅነሳና ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም መሆኑን ለኮንፍረንሱ ተሳታፊዎች ማስገንዘባቸውንም ጠቅሰዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃዎች ተጨማሪ ዋጋ እንዳያስከፍሉን

የጥላቻ ንግግሮች እና ሀሰተኛ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ ዘገባዎች ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለሀገር ሰላምና መረጋጋት ፈተና የሆኑበት እውነታ የአደባባይ ምስጢር ነው። በዚህም እንደ ሀገር ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መንገጫገጮች ውስጥ ለመግባት የተገደድንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

ለውጡን ተከትሎ የተፈጠሩ ፖለቲካዊ ተቃርኖዎችን በሠለጠነ መንገድ በውይይትና በንግግር መፍታት አለመቻላችን ችግሩ ሀገራዊ ገጽታ እንዲኖረው አድርጓል፤ የሀገርን ህልውና ስጋት ውስጥ ከመጨመር ባለፈ ለዘመናት ተከባብሮና ተፈቃቅሮ የኖረውን የሕዝባችንን ማህበራዊ መስተጋብር ተፈታትኖታል ።

እነዚህ የጥላቻ ንግግሮች እና በሀሰተኛ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ ዘገባዎች የበሬ ወለደ ትርክትን ጨምሮ የፖለቲካ አመራሮች ፣ግለሰቦች ፣ቡድኖች እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያነጣጠሩ ፣ ዘመናትን እንደ ሕዝብ ያሻገሩንን የቀደሙ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ እሴቶቻችን እና ብሔራዊ ማንነታችንን የተገዳደሩ ናቸው።

ጽንፈኛ አስተሳሰቦችን በሕዝቡ ውስጥ በማስረጽ በሚፈጠር ሀገራዊ ትርምስምስ የፖለቲካ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን በሚሉ፤ በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገራት በሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች እና ኃይሎች የጥፋት ተልዕኮ የተገዛ ፣ ማንንም ተጠቃሚ ሊያደርግ የማይችል የጥፋት መንገድ ሀገርና ሕዝብን ያልተገባ ብዙ ዋጋ አስከፍሏል ።

በዚህ ሀገርን የማተራመስ የጥፋት መንገድ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ ማደጋችን የሚያሰጋቸው ኃይሎች ተሳትፈውበታል። ከሚያደርጉት የገንዘብ እና የሎጂስቲክ ድጋፍ ጋር በተያያዘም ለጥፋት ኃይሎች ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመሆን ችግሩ እየገነገነ እንዲሄድ አድርጎታል።

በዚህም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ብዙ ሺዎች የሞቱበትና የቆሰሉበት ጦርነት ውስጥ ገብተናል፤በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተፈጠሩ ግጭቶችና የሰላም እጦት በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሀን ዜጎቻችን ለሞትና ለአካል መጉደል ተዳርገዋል፤በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ከቤት ንብረት ተፈናቅለው ምጽዋት ጠባቂ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

"ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን" በሚል ሀገራዊ መነቃቃት ማግስት በጥላቻ ንግግሮች እና በሀሰተኛ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ ዘገባዎች በፈጠሩት ግራ መጋባት ፤በቢሊዮን ብር የሚገመት ሀብት እና ንብረት ለውድመት ተዳርጓል። ችግሩ የፈጠረውን ክፍተት ለመሙላትም ተመልሰን እጃችንን ለምጽዋት እንድንዘረጋ ተገድደናል።

በዚህ ያልተገባ መንገድ ለሀገራቸው ብዙ የሠሩ ባለውለታዎች ፤ለሀገር የነገ ተስፋ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሚተጉ ግለሰቦችን ጨምሮ የትናንት የጋራ ታሪካችን አውራዎች ሳይቀሩ በጥላቻ ንግግሮች እና ዘገባዎች ተብጠልጥለዋል፤ጸያፍ ስድቦች ፣ዘለፋ እና እርግማኖች ደርሰውባቸዋል።

ለዚህም ዘመኑ ያፈራቸው ዲጅታል ማህበራዊ ሚዲያዎች እያበረከቱት ያለው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ቢሆንም፤ ሕዝባችን መረጃዎችን በሰከነ መንፈስ ማየት የሚያስችል ዝግጅት አለመፈጠሩ ችግሩ ግዝፈት አግኝቶ ጥፋቱ እንደ ሀገር ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን እንድንከፍል አድርጎናል።

በተለይም በአውሮፓና በአሜሪካ መኖሪያቸውን ያደረጉ በተቃርኖ የተሞሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ፤በሀገር ውስጥም ከራሳቸው ማህበራዊ ማንነት ጋር የተጋጩ ፅንፈኛ ኃይሎች እና ቡድኖች ፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚደረግን ጽንፍ የወጣ ፕሮፓጋንዳ እንደ አንድ የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው መውሰዳቸው እና ለዚህ የሚሆን ማንነት መላበሳቸው ችግሩን አግዝፎታል።

ከትናንት በስቲያ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ይፋ ባደረገው የስድስት ወራት የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን የተመለከተ ሪፖርት ያመላከተውም ይህንኑ እውነታ ነው። በሀገሪቱ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ እያስከተለ ያለው አደጋ ሰፊና ውስብስብ ሆኗል። ለችግሩም የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ሚና ጉልህ ነው።

ባለፉት ስድስት ወራት የተሰራጩት የጥላቻ መልዕክቶች ለአመጽና ለጥቃት የማነሳሳት፣ የግለሰብን ሰብዕና የመጉዳት፣ የማህበረሰብን ባህልና ወግ በመናድ የሕዝብን አብሮ የመኖር እሴት መሸርሸርን የሚያስከትሉ ሆነው መታየታቸውን አመልክቷል።

የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ እያስከተለ ካለው አደጋ ሰፊና ውስብስብ እየሆነ ከመምጣቱ አንጻር በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ሚና ያላቸውን ማህበራዊ ትስስር አውታሮች፣ መገናኛ ብዙኃን፣ አዋጁን ለማስፈጸም ሚና የተሰጣቸው መንግሥታዊ አካላት፣ የሲቪል ማህበራትና ኅብረተሰቡ የሚጠበቅባቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል።

በተለይም መላው ሕዝባችን የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን መሠረት ያደረጉ ዘገባዎች የሀገርን ሰላምና መረጋጋት ፤የሕዝባችንን የዘመናት አብሮ የመኖር እሴቶች በማጥፋት በአቋራጭ ለመያዝ የሚደረግ ዛሬ ላይ ጭምር ያልተሻገርነው የተበላሸ የፖለቲካ እሳቤ አካል በመሆኑ ለችግሩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፤ተጨማሪ ዋጋ እንዳያስከፍሉን ፈጥኖ መንቃት ይኖርበታል።

ዛሬን በሰላም መኖር ፤በነገም ተስፋ መሰነቅ የሚቻለው ፤ሀገር እንደ ሀገር ጸንታ ስትኖር ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ ከሚሰማቸው የጥላቻ እና የሀሰት መረጃዎች እራሱን መጠበቅ፤ ከቀደሙ የሞራል እሴቶቹ ጋር ያለውን ቁርጠኝነት ማጠንከር ይጠበቅበታል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## "እኔ ካልሠራሁት ልክ አይደለም"

መክሊት ወንድወሰን

እውቅና (Recognition) እና አድናቆት (Appreciation) እንዲሁም ሂስ (Criticism) በልክ ሲሆኑ የሰው ልጅ ራሱን ወደ ውስጥ እንዲመለከት ያስችሉታል። ለተሻለ ሥራ እንዲነሳሳ መስፈንጠሪያ ይሆኑታል። በአንጻሩ ያልተገባ እውቅና እና አድናቆት እንዲሁም ሰዎች መሥራት የሚገባቸውን ያህል እንዳይሰሩ በማድረግ ሞራልን ያኮሰምናሉ፤ ያቀጭጫሉ።

ሊቃውንት "ተፈጥሮ ወናነትን ትጠየፋለች" ይላሉ፤ ብዙ ጊዜ ወናዎች በአግባቡ ሥራቸውን የሚሰሩ እና የማይሰሩ ሰዎችን ለይተው ተገቢውን እውቅና (Recognition ) እና አድናቆት (Appreciation) እንዲሁም ሂስ (Criticism) ከመስጠት ይልቅ በጭፍን መቃወም ወይም መመቅኘት ይቀናቸዋል። የቱንም ያህል ልክ እና ትክክል የሆነ ሥራ ቢሰራም ራሳቸው በቦታው ቢሆኑ እንደማይሰሩት ፤ ከሰሩትም የተለየ ነገር እንደማያደርጉ እያወቁ እኔ ስላላደረኩት ልክ አይደለም ይላሉ።

አሁን አሁን ምክንያት አልባ ሂስ፤ አንድናቆት፤ ጥላቻ እና ተቃውሞ እንዲሁም ምቀኝነት በሀገራችን እየተለመደ የመጣ ይመስለኛል። ምንም ያልሰራን፤ ለሀገር ፖለቲካል ኢኮኖሚ እድገት፤ ጋሬጣን የሆነን ግለሰብ ወይም ቡድን በግብዙ ማድነቅ እና ለሀገር ሁለንተናዊ ለውጥ ሌት ከቀን የሚሰራን ደግሞ በምቀኝንት ማጥላላት፣ መተቸት፣ ማቋሸሽ እና ማራከስ በስፋት እየተስተዋለ ነው። ይህ ትክክል ያልሆነ እና በጊዜ ሊታረም የሚገባው ነው።

በርግጥ አሸናፊዎች ሁሌም አላማቸውን የሚያዩ ናቸው፤ ተሸነፊዎች ደግሞ ወና (ሃሳብ አልባ) በመሆናቸው አላማቸውን ከመመልከት ይልቅ መሰናክሎችን ያያሉ። መሰናክሎቻቸውም በመደርደር ተራማጆችን አላራምድ ማለታቸው የማይቀር ነው። ይህ በእለት ተእለት ሕይወታችን ሳይቀር የምንታዘበው እውነታ ነው።

እንደኔ እንደኔ በአጭር ዘመን የሕይወት ቆይታችን ልናደርግ ከሚገቡን ነገሮች መካከል ዋነኛው ሰዎች ያደረጓቸውን እና የሚያደርጓቸውን መልካም ነገሮችን ሁሉ የማድነቅን ልምድ ማዳበር ነው። ይህም ከአውንታዊ አስተሳስብ የሚመነጭ ነው። አውንታው አስተሳብ ያላቸው ሰዎች ደግሞ ጤነኛ አእምሮ ያላቸው ናቸው። ጤነኛ አእምሮ ያለው ደግሞ ኃላፊነትን መሸከም የሚችል እና በሀገረ መንግሥት ግንባታ አውንታዊ ሚና ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው። ለዚህም ነው ባለቅኔዎች

**ሰናይ ለብእሲ ያወጽኣ ለሰናይት፤**

"እም ሰናይት መዝገበ ልቡ። (በጎ ያለው ከበጎ ልቡ በጎ ነገርን ያወጣል)" ሲሉ ቅኔን መቃኘታቸው።

የማድነቅ ተቃራኒ ማንቋሸሽ ነው፤ ይህም በአብዛኛው ከከፋ ቅናት የሚመነጭ ነው። ቅናት ደግሞ የሚመነጨው ራስን ከሌላው የበለጠ ለማድረግ ካለ ወና ጉጉት ነው። ቅናተኞች የአእምሮ ጤናቸውን ከመጉዳቱ ባሻገር ሰዎችን ጠልፈው ለመጣል አለፍ ሲልም ለመግደል ይነሳሳሉ። በሀገራችንም ፖለቲካል ኢኮኖሚ በስፋት የሚስተዋለውም ይህ ችግር ይመስለኛል።

በሀገራችን የሚገኙ ፓርቲዎች አብዛኛዎቹ ተመሳሳይ ርእዮተ አለም እና ሃሳብ ያላቸው ናቸው ብል ማጋነን አይሆንም። ግን አንድ መሆን ወይም በጋራ መስራት ያቅታቸዋል። ምክንያቱም እነሱ የሚፈልጉት ነገር በሌላኛው ወገን ከተደረገ ነገሩ ልክ እንዳልሆነ ለማሳየት በሚያደርጉት ያልተገባ ፍተጊያ ነው። የሚያስቡትን ሃሳብ በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከመከወን ይልቅ ትከሻ ለትከሻ በመገፋፋት መላላጥን ይመርጣሉ።

እነዚህን እና መሰል አካሄዶች ስመለከት ሰዎች የሚቃወሙት ሰውየውን ነው ወይስ ሃሳቡን? የሚል ጥያቄ እንዳነሳ ያደርገኛል። ጥናት ባላካሂድም ብዙ ሰው ግን የሰውየውን ሃሳብ ሳይሆን እራሱ ሰውየውን የሚቃወም ይመስለኛል። ይሄንንስ ለምን ሰዎች ያደርጋሉ? ብዬ ራሴንም ስጠይቅ ያገኘሁት መልስ አንድም ድፍን ጥላቻ ነው፤ሌላው ደግሞ "ሊደረግ ከታሰበው መልካም ነገር በኋላ፤ የሚመጣው ውዳሴ እና ቅዳሴ ሁሉ ለኔ ነው የሚገባኝ!" ከሚል የቀጨጨ እና የቀነጨረ አስተሳሰብ ነው።

እኔ ይህንን ስል ግን ልክ ያልሆነን ነገር ሁሉ ልንስማማበት ይገባል ከሚል የሞኝ ሃሳብ የመነጨ እንዳልሆነ እንድትገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ። እንደውም እኔ በግሌ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለኝ አቋም ሰው እውነተኛ ነው የሚባለው እውነትን ብቻ ስለተናገረ ሳይሆን ሀሰትንም ሀሰት ነው ብሎ ለመቃወም ድፍረቱ ሲገኝ ነው። ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ለሚሰሯቸው በጎ ተግባራት እውቅና የማንሰጥ ፣የማንደገፍ እና የማናደንቅ ከሆነ ተጠላልፈን ከመውደቅ እና ባለንበት ከመርገጥ ውጭ ምንም ለውጥ ማማጣት አንችልም።

በርግጥ የአብዛኛዎቻችን አስተዳደግ ስንሳሳት በቁጣ፤ ባስ ሲልም በዱላና በስድብ ውርጅብኝ ታጅበን ነው። ላደረግነው መልካም እና በጎ ሥራ "ጎሽ ! ጥሩ አድርገሃል" ብሎ እውቅና የሚሰጥ የአስተዳደግ ሥርዓት ውስጥ አላለፍንም። በዚህ ተጽእኖ የሚፈጠር ባህሪ አብሮን አድጎ! ትምህርት ቤት ተከትሎን ይሄዳል፤ሥራ ቦታ ተከትሎን ይሄዳል፤ የህይወት ዘመን ጥላ ሆኖ ይከተለናል።

"ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" ነውና፤ ይሄ ሽፋኑን "አላመንኩበትም ወይም ነገሩ ልክ አይመስለኝም" የሚል ሃሳብ ውስጡ ከፋት እና ጥላቻን ይዞ ሰዎችን ማድነቅ እንዲያቅተን ያደርጋል። በመጨረሻም ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ እኛም ሳናውቀው ምቀኞች እና ጨለምተኞች ሆነን እናርፈዋለን።

ወናዎች (ሃሳብ አልባ ምቀኞች) ምክንያት አያጡም። ጓደኞቻቸው ትምህርታቸውን 'በጥሩ ውጤት አለፉ' ሲባሉ፤ አስተማሪው ውጤት ጨምሮላቸው ነው ወይም ኮርጀው ነው ይላሉ። "እከሌና እከሊት ቤት ሰሩ።" ሲባል "ጉቦ በልተው ነው።" እከሌ ሹመት አገኘ የእንትን ብሔር አባል ስለሆነ ነው። ይላሉ። ይህ ትክክል አይደለም። ሁሉንም ለማለት ሰዎችን በትክክለኛው ሚዛን መመዘን ያስፈልጋልና።

መንግሥት ለነዋሪዎች ቤት ሲሰራ፤ የተሰራውን ቤት የሰጠው ለራሱ ብሔር ብቻ ነው። የተሽከርካሪዎች መንገድ ጠባብ በመሆኑ እግረኛው እና ተሽከርካሪው እየተጨናነቀ ነው፤ መንግሥት አስፓልት ሊሠራ እና ሊያስፋፋ ይገባል! እንልና መንግሥት እሺ ልስራ ሲል አሁን በዚህ ኑሮ ውድነት አስፓልት ምን ያደርጋል! አስፋልት ምግብ ሆኖ አይበላ? የሚል ትችት እንሰነዝራለን።

ይህ አይነቱ አመለካከት በተለይ ከፖለቲከኞች እና ከምሁራንም ሲነሳ ሳቅ ያጭራል። እኔ በግሌ ይህንን ስል ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ነገሮች የሉም ለማለት ፈልጌ አይደለም። ነገር ግን ለተሰራው በጎ ሥራ አመስግኖ ያልተደረገን እንዲደረግ መጠየቅ እንጂ ሁሉንም መተቸት እና መውቀስ ብቻ አላስፈላጊ እና ለሚደረገው የሀገረ መንግሥት ግንባታ አሉታዊ ጥላ ያጠላል።

ክፉ ሰዎች ነፍሳቸውን በስጋቸው የሚጨቁኑ ናቸው። "የማይገለጥ ሽሽግ የማይታይ ስውር የለም" እንዲሉ ጠቢባን፤ ጊዜው ይረዝም እንደሆነ እንጂ እነዚህ ነፍሳቸውን በስጋቸው የሚጨቁኑ ሰዎች እንከፍ ስራቸው ለሕዝብ እየተገለጠ መምጣቱ የማይቀር ነው። ስለሆነም እኔ ካላደረኩት ልክ አይደለም ከሚል ሃሳብ ወተን እኔ በቦታው ብሆን ከዚህ የተለየ ምን አደርግ ነበር ከሚል ሃሳብ ተነስተን፤ ሁላችንም የስኬት እና የመልካም ነገሮች አድናቂ፤ ጥያቄ ሲኖር በአግባቡ ጠያቂ በመሆን ለሀገረ መንግሥት ግንባታ የበኩላችንን እንወጣ!።

## ነፃ ሃሳብ

# በመከባበር መተባበር

**ቴዎድሮስ ፈለቀ (የኩሽ አሻራ)**

ሀገር ሰሪ ትውልድ አናጭ ከሆኑ የማህበረሰብ እሴቶች ውስጥ መከባበር ቀዳሚው ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ የማህበረሰብ ባህልና ወግ ጥንተ መሰረቷን የማገረች የመቻቻል ደሴት ስለመሆኗ ብዙዎች ይመሰክራሉ። ብዝሀነትን በህብረ-ብሔራዊነት አቅፋ ይዛ፤ በአንድነትና በአብሮነት ወንድማማችነትን ያጸናችበት እልፍ ገጸ ውበት አላት። ክብርና አንቱታን ሰጥተው በፊተኝነት ያቆሙን እኚህ የሀገር ካስማ እሴቶቻችን ባለፈውና ባለው፤ በመጪውም እኛነታችን ውስጥ የጎላ ድርሻ አላቸው።

በባህልና በሥርዓት በአብሮነትም የተማገሩት የመከባበር እሴቶቻችን ሀገር ሰጥተውን፣ ታሪክ አውርሰውን፣ በነፃነትና በክብር በሉዓላዊነትም አጽንተውናል። በዓለም አደባባይ በኢ-ፍትሃዊነት የተረገጠውን የሰው ልጅ ክብር በማስመለስ፣ ዘረኝነትንና የነጮችን የበላይነት ሰው በሚሉት የፍትህ ልኬት የመዘንን፣ የነፃነትን መንፈስ በብዙ መከራና የግፍ አገዛዝ ውስጥ ለነበሩ ወንድማኞችን ያጋባን ነን።

እኚህ የክብር ጸጋዎቻችን ከየት ተነሱ? ብለን ብንጠይቅ መልስ ሊሆን የሚችለው በመከባበር የበለጸገ አብሮነታችን ነው። መከባበር የእኛ የኢትዮጵያውያን ስምና መገለጫ ሆኖ ከዘመን ዘመን ተሻግሯል። ይሄ የማንነት መልክ እኔን ከእናንተ እናንተንም ከኔና ከሌላው የደባለቀ፣ የፍቅር፣ የክብር፣ የፍትህና የሚዛናዊነት ሰው የመሆንም ውርስ ነው። እንደ ሀገር ገዝፈንና ተንሰራፍተን ብኩርናን ስንቸር በመተባበር በኩል አልፈን ነው።

የእኛ ከሆኑ የድልና የገድል ስሞቻችን መሀል በመከባበር መተባበር የሚለው ቀዳሚው ነው። በፍቅር የተቀለሙ ብዙ ወርቃማ ስሞች ቢኖሩንም እንደ መከባበርና መተባበር መሳይ ብዙሀነታችንን የሚያገዝፍ ስም ግን የለንም። ጸንተንና በርትተን ዛሬ ላይ የቆምነው የአንተ የእኔ በሌለው በዚህ ስም ነው።

የስልጣኔ ቀዳማይ የተባልነው በዚህ የጋራ ቀለማችን በኩል ነው። ይሄ የጋራ ስም የጋራ ታሪክ፣ የጋራ ሀገር፣ የጋራ እሴት፣ የጋራ ማንነት፣ የጋራ ሥርዓት፣ የጋራ ወግና ባህል ሰጥቶን ኢትዮጵያዊ አስብሎናል። እንደሀገር በአብሮነታችን ስር የተንጸባረቁ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉ እልፍ ሥነ ቃሎች ያሉን ሕዝቦች ነን።

ለአብነት ያክል ብናነሳ እንኳን ከአንድነታችን የተወለዱ እንደ ‹ድር ቢያብር አንበሳን ያስር፣ ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ› ዓይነት ሥነ ቃሎችን መጥቀስ እንችላለን። ሌላው ከዚህ ውህድና ድብልቅ ሕዝባዊነት ተነስቶ ማንነታችን እስከመሆን የደረሰ፣ ኢትዮጵያና አንድነት ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳ በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ‹ኢትዮጵያዊነት መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይቀይራልን? የሚል ትርክት ባለቤት መሆናችን ነው ።

እኚህ ከላይና ከታች የተገለጹ ዓለማዊና መንፈሳዊ አብሮነትን ገላጭ ቃሎች በአብሮነት ምን ያህል እንደጀገንንና እንደበረታን ከመጠቆማቸውም በላይ አንድ ሆኖ ከመቀጠል ሌላ አማራጭ እንደሌለንም የሚያወሱ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስሟ ከአርባ በላይ የተጠቀሰው ሀገራችን ለፈጣሪ ምን ያህል ቅርብ የሆነ ጥንተ መሠረት እንዳላት የሚጠቁም ነው።

አንድ ወቅት ላይ የነበሩን፣ ለሌሎች ሰጥተን ያካፈልናቸው የሰላም፣ የአንድነት፣ የመከባበር እሴቶቻችን አሁን ላይ ተሸርሽረዋል። እንኮራባቸው የነበሩ የፍቅርና የወንድማማችነት መንፈሶቻችን በነጣጣይ ትርክቶች ተቀይረው አስጊ ደረጃ ላይ ደርሰናል። ሰላም ፈላጊ ከሆንን ቆይተናል።

አንድነት ርቆን በዘርና በብሔር ከተቧደንን ሰንበትበት ብለናል። መተሳሰባችን ወደስጋትና ወደእርስ በርስ መፈራራት ተቀይሮ ከወንድሞቻችን ጋር የማንኖር እስኪመስለን ድረስ በስጋት ውስጥ ነን። ኢትዮጵያዊነትን ከማስቀጠል ይልቅ የአንድ ወገንን የበላይነት ለማስፈን የሚታትሩ ፖለቲከኞችም ተፈጥረው ፈተና ሆነውብናል።

**ሌላው ከዚህ ውህድና ድብልቅ ሕዝባዊነት ተነስቶ ማንነታችን እስከመሆን የደረሰ፣ ኢትዮጵያና አንድነት ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳ በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ‹ኢትዮጵያዊነት መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይቀይራልን? የሚል ትርክት ባለቤት መሆናችን ነው**

ተነጋግሮ ከመግባባት ይልቅ ጦርነትን እንደመፍትሔ በመውሰድ ዛሬም እንደ ትውልድ ያልተገባ ዋጋ እየከፈልን ነው። የአባቶች የማስታረቅ፣ የሃይማኖት መሪዎች የግሳጼ ሚናቸው ደብዝዞ ትውልዱ ሀይ ባይ እያጣ ነው። ከአንድ ቦይ መንጭተን እየፈሰስን የእኔ የአንተ መባባል ጀምረናል። በአንድ ቅርንጫፍ ላይ አብበን መገፋፋታችን ልቋል። በብሔርተኝነትና በጎጠኝነት ሰብዓዊነታችን እየሸሸን ነው።

ባለመደማመጥና ባለመነጋገር በትንሽ ቅራኔ ትልቅ ቤታችንን ስጋት/አደጋ ውስጥ ከትተን አልፈናል። በአንድ እንብላ፣ በአንድ እንጠጣ የነበርን ሕዝቦች ገበታ ለያይተናል። ለዚህም የመጀመሪያው ተጠያቂዎች ፖለቲካውና ፖለቲከኞቻችን ናቸው። የፖለቲካ አስተሳሰብ በአንድ ሀገር ላይ የሥርዓት፣ የብዙሃነት፣ የተሀድሶ፣ የለውጥና የነውጥ መሠረት መሆን ይችላል።

የትኛውም ፖለቲከኛ በሃሳቡ በኩል ሀገርን እንደፈለገ አድርጎ መፍጠር ይቻለዋል። ትውልድም የዚህ አስተሳሰብ ውጤት የመሆን እድሉ የሰፋ ነው። እንደአለመታደል ሆኖ የእኛ ሀገር ፖለቲካ ከለውጥ ይልቅ ነውጥ ላይ ያተኮረ ነው። የሕዝብን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ የራስን ፍላጎት በሕዝብ ላይ በመጫን ተወዳዳሪ የሌለው ነው።

በሃሳብ እና በኢትዮጵያዊነት የበሰለ ሳይሆን በእልህና በቂም በቀል ያረረ ነው። ያ ያደረና የዋለ እልህና በቀል በብሔርና በራስ ወዳድነት ቀርቶ ከኢትዮጵያዊነት ሸሽጎናል። መሸሸግ ብቻ አይደለም የብሔር ካባ ለብሰን እርስ በርስ እንድንፈራራም አድርጎናል። ዛሬ ላይ የተፈጠሩብን ይሄን መሰል አጓጉል ነገሮች ከፖለቲካው ምህዳር የተፈናጠሩ ነውሮች ናቸው።

ፖለቲካው ሃሳብ በሌለው ልብና አእምሮ ከመጣንበት የኢትዮጵያዊነት ሥነልቡና አሸሽቶ የዘረኝነት እድፍ ላይ ጥሎናል። ተያይዘን ካቆምነው ሰንድ ታሪክ ውስጥ አጉድሎና ጨምሮ የመጣንበትን እንድንፈራ አድርጎናል። በአንድ የበላንባቸው ፎሌና ሸክናዎቻችን ተወርውረው፣ በአንድ የተቀመጥንባቸው ጥላዎቻችን ተመንጥረው የሃሩር ሲሳይ እየሆኑ ነው። ግጥምጥም ኮቴዎቻችን መለያየት ገብቶባቸው እዚያ እና እዚህ ተሰምረዋል።

ከሕዝብ እውነት ይልቅ ለራስ እውነት ፊተኛ በመሆን ብዙሃነትን ወደ ብሔርተኝነት አውርደናል። ኢትዮጵያን በሚያሽር የእርቅና የተግባቦት መድረክ ላይ ከመቆም ይልቅ ቁርሾ በማስቀመጥ ትውልዱ እየተነቋቆረ እንዲኖር ሃሳብ አልባ፣ እርቅ አልባ፣ ምክክር አልባ ምህዳርን ለመፍጠር ሞክረናል።

የፖለቲከኞቻችንም የርዕዮተ ዓለም መነሻ ሀገር፣ ሕዝብ፣ ትውልድ እና የጋራ ትርክት ሳይሆን የራስን ፍላጎት በሕዝብ ላይ መጫን ነው። የብቻ ትርክት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። የብቻ ትርክቶች ደግሞ የመጣንበትን፣ ያደግንበትን፣ ባለታሪክ የሆንበትን እና በአንድነት የቆምንበትን የጋራ እውነት ወደ እኔነት የሚለውጥ ነው።

ሁለተኛው በተረት ተረት ሕዝብን ከሕዝብ በማቃረን ትርፍ በሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች የተፈጠረው ተግዳሮት ነው። በእኚህ መሳይ ግለሰቦችና ቡድኖች ብዙ መከራዎችን እንዳለፍን የሚታወቅ ነው። ዳር ቆመው በሚያራግቡት ወሬ፣ እንዲህ ሆነሃል፣ ይሄን ትሆናለህ እያሉ በነጣጣይ ትርክት እንድንፈራራ አድርገውናል። ታሪክ አዛንፈው፣ እውነት አሻፈው ያልኖሩበትን ትላንት እንደትርክት በመውሰድ አንድነታችን ውስጥ መለያየትን ፈጥረዋል፤ አብሮነታችን ውስጥ ጥርጣሬን ነዝተዋል። አንዳንዶች ለአላማቸው ውሸትን እንደእውነት በመውሰድ ጥንተ ብዙሃነታችንን ነቅንቀዋል። አንዳንዶቻችን ሴራቸው ገብቶን በስክነት ኢትዮጵያዊነታችንን አጥብቀናል።

በሶስተኛ ደረጃ የሚነሳው የሚዲያ አሉባልታ ነው። ምንጩ በማይታወቅ፣ የትና ለምን፣ መቼ፣ በማን እንደሆነ በማናውቀው የሚዲያ ወሬ ፍቅራችንን በጥላቻ፣ አብሮነታችንን በመለያየት የቀየርን ብዙ ነን። ከላይ የገለጽኳቸው ሶስቱ መነሻዎች ኢትዮጵያዊነትን አድብዝዘው በእኔነት እንድንቆም አድርገውን እልፍ ዋጋ አስከፍለውናል።

መፍትሔው ሃሳብ አልባ የሆነውን የፖለቲካ ምህዳር ሃሳብ አመንጭ ማድረግ ነው። ፖለቲካችን ሞጋችና በላጭ፣ አንቂና አብቂ ልዕለ ሃሳባውያን የሉትም። ሀገር የፖለቲካ ጽንስ ናት ካልን በኢትዮጵያዊነት እንድናድግ፣ በጋራ ታሪክ ስር እንድንቆም ኢትዮጵያዊ ሃሳብና መልክ ያስፈልገዋል።

ፖለቲከኞቻችን ወደፖለቲከኛ ከመቀየራቸው በፊት ሰው ነበሩ። ሰው ሆነው ሀገር እንዲመሩ፣ ሰው ሆነው ሕዝብ ፊት እንዲቆሙ፣ ሰው ሆነው እንዲሚገቱ፣ ሰው ሆነው ሰው ሰው እንዲሸቱ ልንረዳቸው ይገባል። ለዚህ ደግሞ እኛ ቀድመን የተለወጠ ማንነት ልንገነባ ይገባል።

በአንድ ሀገር የጋራ እሴት የጋራ ማንነት ያህል ዋጋ ያላቸው ናቸው። የእኔ የአንተ የሌለባቸው፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ የማይንጸባረቅባቸው ከኢትዮጵያዊነት መንጭተው ወደ ኢትዮያዊነት የሚፈሱ የጋራ ትውፊቶቻችን ናቸው። በብዙ የተመሳሰልን፣ በብዙ ተቆራኝተን ሀገርና ሕዝብ የሆንን ነን።

ይሄ ማንነት በፖለቲካ ሴራም ሆነ በአሉባልታ አራጋቢዎች እንዳይፈርስ ሆኖ የጸና ማንነት ነው። ስለሆነም በጋራ ከማገርነው ከኢትዮጵያዊነት የሚበልጥ አንዳች እንደሌለ በማሰብ ለአሉባልታና ለወሬኞች ጊዜ ባለመስጠት አብሮነታችንን ማጽናት አለብን።

እንደሀገር አንድነታችንን ለመመለስ፣ በእርቅና በይቅርታ አብሮ ለመጓዝ ኮሚሽን አቋቁመን ነፃና ገለልተኛ ሕዝባዊ ውይይት ለማድረግ እየተሰናዳን ነው። ይሄን መሰሉ አካሄድ ታሪክ በመመለስና አብሮነትን ከማስቀጠል አኳያ እጅግ ዋጋ ያለው፣ ተስፋ ሰጪና መጪውን በበጎ እንድንቃኝ የሚያደርግ ነው። በበጎ ትርክት ዳብረን ቁርሾዎቻችንን ወደ እድል፣ ጥላቻዎቻችንን ወደፍቅር ቀይረን በአዲስ ስም የምንነሳበት ነው።

ብሔራዊ እርቅ ትላንት ዛሬና ነገ የሚዳሰሱበት ከሕዝብ በሕዝብ ለሕዝብ በሆነ ጽንሰ ሃሳብ ነፃ የምንወጣበት የተግባቦት መድረክ ነው። አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ እንደጥሩ አጋጣሚ ተጠቀመንበት ወደኢትዮጵያዊነት ከፍታ የምንመልስበት ነው። ቁርሾዎቻችን ከየትም ይምጡ፣ ለምንም አላማ ማንም ያምጣቸው ከመነሻ እስከመድረሻቸው ድረስ በሕዝባዊ ውይይት እርቅና ተግባቦትን ባስቀደመ አቅጣጫ ታርቀንና ተቃቅፈን የምናልፋቸው ናቸው።

ሃሳብ የዳበረበት፣ ሃሳብ የሚዋጣበት፣ ከምንም በላይ ደግሞ የመፍትሔ ሃሳብ የሚንሸራሸርበት ሀገራዊ ምክክር ያለፈውን አክመን፣ የዛሬን አርመን ነገን የተሻለ ለማድረግ እጃችን ላይ ያለ በጎ እድላችን ነው። በእድላችን ተጠቅመን በአስታራቂ ትርክት አብሮነታችንን የምንመልስበት ወቅታዊ መድረክ ነው።

ሌላው ለችግራችን የመፍትሔ አካል የሚሆነው፤ ለሚዲያ አሉባልታዎች ቦታ አለመስጠት ነው። ማንነቱን ደብቆ ማንም የፈለገውን በሚተፋበት የሚዲያ ዘመን ላይ ነው። ሌሎች የተፉት የሀሰት ወሬ እኛን እንዳያቀያይመን ጨዋና አስተዋይ ሆነን ነገሮችን በእርጋታ መቃኘት ይጠበቅብናል። በገንቢ ትርክት ችግሮቻችንን አክመን ወደፊት ከመሄድ እና አብሮ ከመቆም ሌላ አማራጭ እንደሌለን አያይዘን ልንረዳ ይገባል።

በታሪክ ዳብረን፣ በብዙሃነት አብረን የመጣን ነን። ተሳስረን፣ ተዋልደን፣ በአንድ ገጸ ሰብ ኢትዮጵያዊ የተባልን ነን። በገዘፈ የነፃነት ጥላችን ብዙዎችን በማስጠለል፣ በሰፋ የፍትህ ሚዛናችን ብዙዎችን ባለተስፋ በማድረግ፣ ከወደቁበት በማንሳት፣ ከተናቁበት ቀና በማድረግ ባላደራዎች ነን። በመከባበር መተባበር ምን እንደሆነ ብንጠየቅ የምንመልሰው ብዙ መልስ ያለን ነን። መሀላችን ገብቶ ማንም እንዲያዝለንና እንዲያደነቃቅፈን ባለመፍቀድ አብሮነታችንን እናጽና!።

# ወቅታዊ



ፎቶ፦ ገበበ ገብሬ

# “የመረጃ አሰጣጣችን የተዓማኒነት መጠኑ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል”

**አቶ ፈጠነ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር**

አስቴር ኤልያስ

**የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በእያንዳንዱ ወቅት የሚኖረውን አጠቃላይ የአየር ፀባይ ትንበያ በመስጠት የሚታወቅ ተቋም ነው። መረጃው፤ ያለውን እድልና ስጋት አመላካች በመሆኑ ከሚሰጠው መረጃ በመነሳት የአየር ፀባይ ሁኔታው በሚያመጣው እድል መጠቀም የሚጀምር ሲሆን፣ ከሚመጣው ስጋት ደግሞ በመጠንቀቅ ዝግጅት ይደረግበታል።**

**ከዚሁ ከአየር ሁኔታና የአየር ጸባይ ጋር ተያይዞ አዲስ ዘመን ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍሪካ አህጉር ፕሬዚዳንት ከሆኑት ከአቶ ፈጠነ ተሾመ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጓል። በቆይታውም ስለ አየር ሁኔታና ጠባይ ምንነት፣ ተቋሙ ስለሚጠቀምበት ቴክኖሎጂ፣ የበልግ ዝናብን በተመለከተና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ከአቶ ፈጠነ ተሾመ መረጃ አግኝቷል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- የአየር ትንበያ መረጃ ሲባል የሚያካትተው ምንድን ነው?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የአየር ትንበያ ምንነትን ከመጥቀሴ በፊት የአየር ሁኔታ እና የአየር ጸባይ የሚባሉ ነጥቦች አሉ። የአየር ሁኔታ ሲባል የአጭር ጊዜ ሲሆን፣ በቀኑ ውስጥ የሚለዋወጠውን የአየር ሁኔታ የሚመለከት ነው። የአየር ጸባይ ሲባል ደግሞ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ የአየር ንብረት ሁኔታ ተብለው የሚጠሩት ናቸው። እነዚህን ነገሮች ለመለየት ሁለቱንም አጣምሮ የሚያጠናው ሚቲዎሮሎጂ የሚባለው ነው።

ሚቲዎሮሎጂ ሲባል የአየር ሁኔታንና የአየር ጸባይ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ የሚሰበስበውም መረጃ ከምድር በታች ከአንድ ሜትር ጀምሮ ያለውን የአፈር ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በአካባቢ አየር ውስጥ ደግሞ እስከ 30 ኪሎ ሜትር ድረስ በተለያየ ደረጃ ያለውን የሙቀት መጠን፣ የአየር ግፊት፣ የነፋስ ፍጥነት፣ የዝናብ ሁኔታና መጠንን ነው።

የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ የሚሰጠው በሚቲዎሮሎጂ መረጃ ላይ በመመስረት ነው። መረጃዎቹ ከገጸ ምድር በታች፣ በገጸ ምድርና በካባቢ አየር ውስጥ ያሉ ናቸው። በዚህ ሁኔታ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነውና በባለሙያው ተጠናቅረው በጥሬ መረጃ የሚሰጡ አሉ፤ እንዲሁም ወደትንበያ የሚቀየሩ አሉ።

ስለዚህ ወደፊት እያንዳንዱ ተመራማሪ የአየር ሁኔታንና የአየር ጸባይ መረጃን በተመለከተ ማጥናት የሚፈልግ በሚቲዎሮሎጂ መረጃ ላይ ይመሰረታል። የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በመላ ሀገሪቱ ከአንድ ሺ 300 በላይ የገጸ ምድር የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ያሉትም ለዚህም ነው። ከዛ በተጨማሪ በዘመናዊ መልክ አውቶማቲክ የሚቲዎሮሎጂ መሰብሰቢያ የሚባሉ በየ15 ደቂቃ ልዩነት ዋናው መሥሪያ ቤት ከሚገኘው ሰርቨር ጋር ተገናኝተው የሚሰጡ መረጃዎች አሉን።

ሌላው የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር የሚባለው ደግሞ 250 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ያለውን የሚቲዎሮሎጂ መረጃን የሚሰበሰብ ነው። ስለዚህ ሽፋኑ እንደጣቢያው ወይም እንደ መሳሪያ ዓይነት ልዩነት አለው። እንዲህም ሲባል አንደኛው ዘመናዊ በሆኑ መሳሪያዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሲሆኑ፣ ሌላው ደግሞ በሰው መረጃ አቀባይነት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው። እነዚህ ተደራሽነታቸው ውስን የሆኑ ቦታዎች ላይ ነው።

ሚቲዎሮሎጂ ትንበያ ከመስጠቱ በፊት መሠረት የሚያደርገው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ላይ ነው። መረጃ ከሌለው ትንበያ መስጠት አይችልም። ስለዚህ የሀገር ውስጥ መረጃን ያያል፤ ሌላው የአየር ጸባይና ሁኔታ በሀገራት ዳር ድንበር የሚወሰን አይደለም። ተሻግሮ የሚሄድ ነው። ስለዚህ ሕንድ ውቂያኖስ፣ አትላንቲክ ውቂያኖስ፣ በቀይ ባህር፣ በሰሃራ በረሃ እንዲሁም ባህረ ሰላጤ አካባቢ ያለው የአየር ጸባይ የእኛን የበጋ፣ ክረምት እና የበልግ ዝናብን ሁኔታ በመጨመርም ይሁን በመቀነስ ደረጃ ወሳኝ ሚና አላቸው። ይህ ማለት ከኢሊኖ እና ላሊና ጋር የሚያያዝ ነው። በመሆኑም ይህን ሁኔታ ለሀገር ውስጥ መረጃ እንደ አንድ ግብዓት እንጠቀማለን።

በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ትንበያ ማዕከላት የሚተነበየውን በሕንድ ውቂያኖስ፣ በአትላንቲክ ውቂያኖስ እንዲሁም በቀይ ባህር ላይ የሚታየው የባህር ወለል መሞቅና መቀዝቀዝን ኢትዮጵያ ከግምት ውስጥ ታስገባለች፤ እንዲሁም በተመሳሳይ ዓመታት ከአየር ጸባይ ጋር ተያይዞ የተከሰተውንም ከግምት በማስገባት ከየትኞቹ ዓመታት ጋር ይመሳሰላል በማለት የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ትንበያ እንሰጣለን። የአጭር ጊዜ ትንበያ የምንለው ከሰዓታት ጀምሮ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ያለውን መረጃ ነው። የመካከለኛ የሚባለው ደግሞ ከሶስት ቀን እስከ አስር ቀን ያለውን ሲሆን፣ የረጅም ጊዜ የሚባለው ከአንድ ወር ጀምሮ እስከ ወቅት ድረስ ያለው ነው። እኛም መረጃ የምናደርሰው በሶስቱ የጊዜ ሰሌዳዎች ዙሪያ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ የምንሰጠው የረጅም ጊዜ ትንበያውን ነው።

**አዲስ ዘመን፡-እርስዎ ባሉት መልኩ የተጠናቀሩትን የአየር ትንበያ መረጃዎች ለሚመለከተው አካል በአግባቡ ማድረስ ፋይዳው የት ድረስ ነው ይላሉ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው። በዚህች ምድር ላይ ወሳኝ ከሆኑ ነገሮች አንዱ የአየር ሁኔታ ነው። ስለዚህ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አንደኛ ሕይወትንና ንብረትን ከአደጋ ለመታደግ ወሳኝነት አለው። ሕይወትንና ንብረትን ከአደጋ ለመታደግ ስንል አንዳንድ ጊዜ ድርቅ፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከከፍተኛ ዝናብ የተነሳ የጎርፍ አደጋ ያጋጥመናል። ሁለቱም በአግባቡ ካልተመሩ በሕይወትና ንብረት ላይ የራሳቸው የሆነ አደጋ ያሳርፋሉ።

ለምሳሌ በኢትዮጵያ የተከሰቱትን የድርቅ ዓመታት ወደኋላ መለስ ብለን ብናይ በቅርቡ የቦረና፣ የጉጂ፣ የባሌ ቆላማ አካባቢዎች ላይ እና ሱማሌ ያጋጠመው ይጠቀሳል፤ በተለይ የቅርቦቹን የድርቅ ክስተት ስናጤን ለአምስት ተከታታይ ወቅት ዝናብ ሳያገኙ በመቅረታቸው የመጣ ነው። በዚህ ሳቢያ ደግሞ የአርብቶ አደሩ እንስሳት በብዛት አልቀዋል።

ድርቅ የሚያጋጥመው ለምንድን ነው? የሚለውን በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በምናይበት ጊዜ የኢትዮጵያን የአየር ሁኔታ የሚወስኑ አስቀድሜ የጠቀስኳቸው የሕንድ ውቂያኖስ እና የአትላንቲክ ውቂያኖስ ላይ የተከሰቱት ክስተቶች በመኖራቸው ናቸው። ይህም ማለት የባህር ወለል ሙቀት መጨመርና መቀነስ ነው። ስለዚህ የኢሊኖ እና ላሊና ክስተት በምናይበት ወቅት በተለይም ኢሊኖ በጋ እና ክረምት ላይ በሚከሰትበት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የዝናብ መጠን እንዲኖር ያደርጋል።

እንደሚታወቀው በሀገራችን ሁሉም አካባቢዎች የክረምት ዝናብ የሚያገኙ አይደሉም፤ የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍል በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፤ በጋ ደግሞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። ለቦረና፣ ጉጂ፣ ሱማሌና በቀድሞ አጠራር የደቡብ ክልል በተለይ የኮንሶና ቡርጂ አካባቢዎችን ብንወስድ በልግ ዋንኛ በጋ ደግሞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። የክረምት ወቅት ደግሞ ለእነርሱ ደረቅ ጊዜ ነው። በመሆኑም የክረምት ወራትን እንደተቀረው የሀገሪቱ ክፍል አይጠብቁም።

የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢ እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍልን ደግሞ በምናይበት ጊዜ ክረምት ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። የተወሰነ ሰሜን አጋማሽ ምሥራቃዊ ክፍል የእነራያና ወሎ አካባቢ በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው። ስለዚህ ለእነርሱ በጋ ደረቅ ወቅት ነው። በአካባቢያቸው በበጋ ወቅት ዝናብ ቢዘንብ የሚባለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ነው። የምዕራብ አጋማሹ እንደ እነኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላ ያሉ አካባቢዎች ደግሞ በዓመት ውስጥ እስከ ስምንት ወራት ድረስ ዝናብ የሚያገኙ ናቸው። በበልግ ወቅት ዝናብ ብዙ አይጠበቅም።

አሁን ወቅቱ የበልግ ነው፤ በልግ ደግሞ በኢሊኖ ተጽዕኖ ስር ስለሆነ ቦረና ላይ የምናው ዓይነት ድርቅ አይኖርም። ስለዚህ ትንበያውን ቀድመን በምንሰጥበት ጊዜ ሁሉም ይዘጋጃል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን፣ የግብርና ሴክተሩ፣ የውሃ ሴክተሩ እንዲሁም የጤና ሴክተሩ ሲሆኑ፣ እነዚህም ዝግጅት ያደርጋሉ። ለዚህም ሲባል ባለፈው ጥር ወር ከየሴክተሩ ለተውጣጡ ወደ 300 አካላት ከየካቲት እስከ ግንቦት የአየር ትንበያ መረጃ ሰጥተናል። ለሁሉም ሴክተር እንደየሥራው ባህሪ የተለየ ጥቅም ያለው በመሆኑ እንደሚያገኘው መረጃ ዓይነት የየራሱን ዝግጅት ማድረግ ያስችለዋል።

መረጃው በተለይ በቅርቡ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የተጀመረ የበጋ ስንዴ ሥራ በአግባቡ ለማስኬድ ያስችል ዘንድ መረጃን በመጠቀም ከወዲሁ ውሃ መያዝ የሚገባ ከሆነ በመያዝ ጭምር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ማለት ነው። ጤና ላይ ለምሳሌ የወባ ሥርጭትን አስመልክቶ የተተነበየውን መረጃ ከግምት በማስገባት ሴክተሩ እንዲዘጋጅ እድል ይሰጠዋል። በዚህ መሠረት ከግብርና፣ ከውሃ፣ ከጤና፣ ከአደጋ ስጋት አመራር ጋር የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕቀፍ ብለን የጋራ ስምምነት ተፈራርመናል። ስለዚህ በየጊዜው መረጃዎቻችንን ይጠቀማሉ። ይህን በማድረጋቸው አንደኛ የአደጋ ተጋላጭነትን ይቀንሱበታል፤ ሁለተኛ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋሉ።

ውሳኔ ሰጪ አካላት በክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የብሔራዊ የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት ላይ ብቻ ተነጋግረው አያበቁም። ታች ያለው ላይ ችግር እንዳይሆን የክልል ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የሚሳተፉበት፣ የሚመለከታቸው የአደጋ ስጋትና የግብርና ቢሮ ኃላፊዎች የተገኙበት ውይይቶች ይደረጋሉ። በዚያ ውይይት ወቅት ሚቲዎሮሎጂ መረጃ ያቀርባል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጎርፍ በሚበዛበት ወቅት “የከፍተኛ ተፋሰስ አስተዳደር ምክር ቤት” በሚል ስያሜ የሚታወቅ ተቋም አለ፤ ይህ ተቋም ጎርፍ የሚያጠቃቸውን አካባቢዎች ታሳቢ በማድረግ ለምሳሌ አዋሽ ከመነሻ ጀምሮ እስከ መድረሻ እንዲሁም የጣና በለስ፣ ባሮ አኮቦ፣ የገናሌ ተፋሰሶች እነዚህ ችግር እንዳያመጡ አቅጣጫዎች የሚሰጡበት ሁኔታ አለ። በተለይ የሚከተሉት ስትራቴጂ ሕዝብ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ቀድሞ የመከላከል ነው።

ሌላው የትንበያ ፋይዳው ለየኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ነው። ለባለስልጣኑ የትንበያ መረጃ የሚሰጠው የረጅም ጊዜ ትንበያ ተጠብቆ ሳይሆን ከሰዓታት ጀምሮ እስከ አጭር ቀናት ድረስ ነው። ተቋማችን ካለው የሰው ኃይል ውስጥ ወደ አንድ መቶ የሚጠጋ የሰው ኃይል ያለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ነው። ስለዚህ የትኛውም አውሮፕላን ከመነሳቱ በፊት እና ከማረፉ በፊት እንዲሁም በበረራ ወቅት የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ይደርሰዋል። እንደሚታወቀው ብዙ ጊዜ የአውሮፕላን አደጋ የሚከሰተው 70 በመቶው ከአየር ጸባይና ሁኔታ ጋር በተያያዘ ነው።

እኛ የባህር በር ስለሌለን ነው እንጂ ማሪን ሚቲዎሮሎጂ ተብሎ በመርከቦች እና በጀልባዎች ላይ ሚቲዎሮሎጂ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ይተከሉና ከፍተኛ የባህር ላይ ሞገድ በሚነሳበት ወቅት መረጃ ይሰጣሉ፤ ለምሳሌ ሞገዱ ምን ጊዜ ይመጣል? የሚለውን መተንበይ ስለሚያስፈልግ ለዛ ሲባል መረጃው ይሰጣል። በኢትዮጵያም በኩል የባህር በሩ ከተሳካ በዘርፉ ጥሩ የሆነ መረጃን በማቀበል ሱማሊያን ማገዝ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ የሚያደርሰው መረጃ ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ጠቀሜታው ለግብርና ዘርፉ ብቻ እንደሆነ ይታሰባል። ይህን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** በርግጥ መረጃው ለበርካታ ዘርፍ ወሳኝ ነው። ለግብርናው፣ ለጤናው፣ ለአደጋ ስጋት አመራሩ እና ለሌሎችም ሴክተሮች ጠቀሜታው የጎላ ነው። ለምሳሌ ለአደጋ ስጋት አመራሩ በቀጣዩ ዓመት ምን ያህል ተረጂ እንደሚኖረውና ሰብዓዊ ድጋፍ ለመስጠት ያመቻቸው ዘንድ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ያስፈልገዋል። በተመሳሳይ ከውሃ አስተዳደር ጋር ተያይዞ ለምሳሌ በግድቦቹ ያለው የውሃ መጠንን ይዞ ለማቆየትም ሆነ ለማስተንፈስ መረጃው ወሳኝ ነው። ሌላው ደግሞ የአየር በረራ አገልግሎትም እንዲሁ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ መረጃ ለሁሉም አስፈላጊ ቢሆንም፤ እነዚህ የጠቀስኳቸው የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ በጣም ወሳኝ በሆነ መንገድ የሚያስፈልጋቸው ሴክተሮች ናቸው። በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅትም የአየር ጸባይ አገልግሎት ማዕቀፍ በሚል የተፈራረምናቸው ከእነዚሁ ሴክተሮች ጋር በመሆን ነው።

በተጨማሪ ደግሞ ከተሞችም እንዲሁ የኮንስትራክሽን ዘርፉ እንዳይስተጓጎል መረጃው አስፈላጊው ነው። ለምሳሌ የኮንስትራክሽን ዘርፉ አንድን ሕንፃ በሚያንጽበት ወቅት ፈጥኖ ከመሠረቱ መውጣት ያለበትን የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ መረጃው ሊያመላክተው ይችላል። እንዲሁ የመንገድ ሥራም ሊሆን ይችላል የአየር ሁኔታውና ጸባዩ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍበት ስለሚችል ቀድሞ ለመጠንቀቅ መረጃው ወሳኝ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ መረጃ ፖሊሲ እስከማስቀየር የሚደርስ እንደሆነ ይነገራልና እዚህ ላይ ማብራሪያ ቢሰጡን?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ለፖሊሲ አውጪዎች ለምሳሌ አንድ ሀገር የኢነርጂ ፖሊሲ ይኖረዋል፤ የእኛ የኢነርጂ ምንጭ ታዳሽ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

ከገጽ 7 የዞረ

# “የመረጃ አሰጣጣችን የተዓማኒነት መጠኑ...

ኢነርጂ የሚባለው ነው። ይህ ታዳሽ ኢነርጂ ደግሞ መሠረት ያደረገው አንዱ ውሃ ላይ ነው። እንዲያውም ኃይል ሲታሰብ የእኛ ሀገር በብዛት የተመሰረተው ውሃ ላይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ንፋስ ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ የእንፋሎትና የፀሐይ ኃይል ነው። እነዚህ የኃይል ምንጮች ሁሉ የሚቲዎሮሎጂን መረጃ የሚፈልጉ ናቸው።

ስለዚህ ትንሽ ሰፋ የሚል ስለሆነ ውሳኔ ሰጪ አካላት ብዙ ጊዜ እቅዶቻቸውን እንደየሁኔታው ይከልሳሉ። ለምሳሌ ዘንድሮ ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ከሚሰጠው መረጃ በተጨማሪ በሚከሰተው የዝናብ እጥረት ውስጥ ጣልቃ እየገባን መምጣት ጀምረናል። ለምሳሌ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ጋር በመነጋገር ዳመናን ወደዝናብ (ክላውድ ሲዲንግ ቴክኖሎጂ) የመቀየር ማለትም ዳመናን የማበልጸግ ቴክኖሎጂን መጠቀም ጀምረናል። ይህ ማለት ሁሉም ዳመና ዝናብ ሰጪ ነው ማለት አይደለም። ቁልል ደመና ተብሎ የሚጠራው መኖሩ ሲረጋገጥ ነው። ስለዚህ ይበተን የነበረ ዳመና በዝናብ መልክ እንዲወርድ ይደረጋል፤ ይህንን ላለፉት ሶስት ዓመታት ተግባራዊ አድርገናል።

ብዙ ጊዜ ከአረብ ሀገር ባለሙያዎች ይመጡ የነበረው በልግ ላይ ነው። በዚህ ዓመት ግን አልጠራናቸውም። ምክንያቱም ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚጠበቅ ስለሆነ ነው። ከዚህ የተነሳ የእቅድና የአቅጣጫ ለውጥ አድርገናል ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት እንኳ በአንዳንድ ቦታ ላይ ጎርፍ የሚያስከትል ዝናብ ይኖራል ብለን ስለጠበቅን በዚህ ላይ ዳመናን ወደዝናብ የመቀየር ቴክኖሎጂን መጠቀሙ አግባብ አይደለም። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም በፓርላማ ላይ ዘንድሮ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የምንጠብቅ ስለሆነ ዳመናን የማዘነቡ ነገር እንደማይኖር አስረድተዋል። ስለዚህ የእቅድ ለውጥ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

ለምሳሌ መሬታችንን በመስኖ ማልማት ቢፈለግ በቂ የሆነ የዝናብ ውሃ ስለሚኖረን ሌላ ፍሊጋ አንሄድም። በሌላ በኩል ደግሞ ምርት አሰባሰብ ላይ ብክነት እንዳይመጣ የመረጃው በአግባቡ መድረስ ሚናው ላቅ ያለ ነው። በቂ መረጃ የማይኖረን ከሆነ ምርት ሊባክን ይችላል፤ መረጃው ካለ ግን ተማሪዎችንም ሆነ ሌላውን የኅብረተሰብ ክፍል በማስተባበር ምርት እንዲሰበስቡ ማድረግ ይቻላል። በዋናነት የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜን ትንበያን በመጠቀም እቅዶቻቸውን መከለስ ይችላሉ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አኳያ ምን ያህል ርቀት ተጉዟል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እንደሚታወቀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቴክኖሎጂው እየተለወጠና አቅሙንም እያጠናከረ መጥቷል። የእኛም ተቋም ከቴክኖሎጂ አንጻር አቅሙን እያጎለበተ የመጣ ነው። ከአንድ ሺ 300 በላይ በሰው ኃይል መረጃ የሚሰበሰብባቸው ጣቢያዎች አሉን። የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያዎች በየትኛውም ዓለም ስታንዳርዱን የጠበቀ በመሆኑ ተመሳሳይ ነው። ስታንዳርዱን የሚወስንልን የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያም የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል ናት። በመሆኑም ከዚያ ወጣ ያለ ብዙ አሰራር አይኖረንም።፡

ነገር ግን ቴክኖሎጂው በየሶስት ሰዓቱ ልዩነት ተመልካች እየሔደ መረጃ የሚሰበስብበትን አሰራር ለማስቀረት ቴክኖሎጂ ወሳኝ ነው። ሚቲዎሮሎጂ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ በሰው የሚሞላ መረጃን ሲጠቀም ነበር። ይህ እኛ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር የሚሰራበት ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ወቅት ዓለም ወደዘመናዊነት እየተሸጋገረ ነው። ለዚህ ማሳያ ከሆኑት አንደኛ ሰው አልባ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ (Automatic Weather Station) የሚባለው ሲሆን፣ ከየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ ለምሳሌ ጎዴ ላይ ወይም ሁመራ ጫፍ ተተክሎ በ15 ደቂቃ ልዩነት እኛ ሰርቨር ላይ መረጃውን የሚያደርስ ነው። እንዲህ ዓይነቱን መሳሪያ 300 ጣቢያ ላይ ተክለናል።

ሁለተኛው ደግሞ የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር ነው። ቀደም ሲል ራዳር አልነበረንም። አንደኛ ከዋጋ አንጻርም በጣም ውድ ነው። አንድ የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር እስከ 130 ሚሊዮን ብር ይፈጃል። ስለዚህ አንድ ሻውራ በሚባል ቦታ ጣና በለስ አካባቢ ያለውን የጎርፍ ክስተትን እንዲሁም ለዳመና ማዝነብ የሚሆኑ የዳመና ዓይነቶችንም ለመለየት የሚጠቅመን መሳሪያ ነው።

ከዳመና ማዝነብ ጋር የመጀመሪያውን ሙከራ ያደረግነው ወደጣና በለስ አካባቢ ነው። አካባቢው የተመረጠበት ምክንያት ራዳሩ እዛ አካባቢ ስላለ ነው። መሳሪያው ቀደም



ሲል የተተከለ ቢሆንም በኋላ ላይ ግን ከተባበሩት አረብ ኢምሬቶች ከመጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወደሥራ በማስገባት ከአራት ዓመት በፊት እንደየሁኔታው እየታየ ጠቀሜታ ላይ እንዲውል ማድረግ ችለናል።

በኋላ ላይ ደግሞ ከፊንላንድ መንግሥት ጋር በመተባበር በአሁኑ ወቅት ተጨማሪ ሶስት የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር በተለያየ የሀገሪቱ አካባቢ ለመተከል ወደየቦታው በመሔድ ላይ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር አራት ራዳር ማድረስ ተችሏል። ይህ ራዳር በ250 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውስጥ ያለውን የዝናብ መጠን፣ ሊመጣ ያለውን የጎርፍ አደጋ፣ ሊበለጽግ የሚችል የዳመና ዓይነት ለመለየት እንዲሁም ለአውሮፕላን በረራ ስላለው የአየር ሁኔታ ምልክት የሚያሳይ ነው። ይህ መሳሪያ ሁለተኛው የዘመናዊነት መገለጫ ነው።

ሌላው የከፍታ አየር መመዝገቢያ ራዲዮሶንዴ ባሉን (Radiosonde balloon) የሚባለው ነው። መሳሪያውን ከባቢ አየር ውስጥ በመልቀቅ ያለውን መረጃ እየመዘገበ እንዲልክ የሚደረግ ነው። በተለይም ምን ዓይነት የእርጥበት ዳመና አለ? ምን ዓይነት የሙቀት መጠን አለ? ምን ዓይነት የንፋስ ፍጥነትና አቅጣጫ አለ? የሚለውን ይመዘግባል። ወደ ከባቢ አየር ለሚለቀቀው ባሉን እስከ 300 ዶላር ወጪ ያስወጣል።

ሌላው የሳተላይ መረጃ የሚባለው ነው። እንደገና ከዓለም አቀፍ ሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት ጋር በመተባበር መረጃዎችን በነፃ እናገኛለን። ምክንያቱም ለዚህ ስምምነት አለን። ለዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባልነት ዓመታዊ መዋጮ እናዋጣለን። ከኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ጋር በመነጋገርም ሳተላይቶችን ማምጠቅ ችለናል።

ለአየር መንገድ ከራሱ ባህሪ አንጻር በአራት ዓለም አቀፍ በረራን በሚያስተናግዱና 18 የሀገር ውስጥ በረራን ለሚያስተናግዱ የአየር ጣቢዎች ለእያንዳንዳቸው አውቶማቲክ የአየር ሁኔታ መመልከቻ ሥርዓት (Automatic Weather Observing System) የሚል ስያሜ ያለው መሳሪያ ተተክሏል። ይህ መሳሪያም ዘመናዊ ነው። ከዚህ በፊት መረጃው ይሰበሰብ የነበረው በሰው ነው። አየር መንገዶቹ በሚቋቋሙበት ወቅት በጋራ የምንሰራው እነዚህን ነገሮች አስበን ነው። ስለዚህ የመረጃ አሰጣጣችን የተዓማኒነት መጠኑ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል።

በሰው ኃይሉ ላይም የተሠሩ ሥራዎች አሉ። ለምሳሌ በዚህ በጀት ዓመት ብቻ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ወደ 61 ባለሙያዎችን በሁለተኛ ዲግሪ አስመርቀናል። እንደገና ደግሞ በቻይና እና በሌሎች ሀገራትም ጭምር ወደ ሰባት የሚሆኑ ባለሙያዎች የሶስተኛ ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ኢንስቲትዩቱ በአንድ በኩል አገልግሎት ሰጪ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምርምር ተቋምም ሆኖ እንዲሰራ በቴክኖሎጂ፣ በሰው ኃይል አቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢንስቲትዩቱ ከሚቲዎሮሎጂ አንጻር ከሀገራት ጋር ያለው ትስስር ምን ይመስላል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እንደሚታወቀው ያለን ትስስር ከሚቲዎሮሎጂ አንጻር ነው። የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል ነን። በዚህ ድርጅት ውስጥ ሚናችን ከፍ ያለ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እና በቀጣናው ላይ ያላት ተሳትፎ ትልቅ ነው።

በዚህ መሠረት የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ድርጅትን በመወከል አባል በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ። ድርጅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው 27 መቀመጫ ነው። ከዚህ ውስጥ አፍሪካ ዘጠኝ ወንበር አላት። ከዘጠኙ አፍሪካ ሀገራት ወንበር ውስጥ ደግሞ አንዱ የኢትዮጵያ ነው። እኤአ ከ2015 ጀምሮ ቦታችንን ሳንለቅ በየአራት ዓመቱ የተካሔዱትን ያለፉትን ሁለት ምርጫዎች ማሳካት ችለናል።

ሌላው ደግሞ በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ውስጥ ስድስት ቀጣናዎች አሉ። ቀጣና አንድ ተብሎ የሚጠራው አፍሪካ ሲሆን፣ አውሮፓ፣ እስያ፣ ሰሜን አሜሪካና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው። እርስ በእርስ እየተመካከሩ ከተቻለ በስምምነት፤ ካልሆነ በድምጽ ብልጫ ይመረጣል። እንደ አፍሪካ ከተወሰደ ብዙ ነገሮቻችንን እንድንጨርስ ያደረግነው በስምምነት ነው። በተለይም በምርጫው አካሄድ እጩዎቻችንን ተስማምተንበት ያቀረብንበት መንገድ አውሮፓን ዴሞክራሲ ያስተማርን የሚያስብለን ነው።

በቅርቡ የዛሬ ዓመት ኢትዮጵያ ላይ እንዲሁ የአፍሪካ ቀጣና ምርጫ ተካሒዶ ነበር። ምርጫውን ለቀጣዮቹ አራት ዓመታት ከሥራ አስፈጻሚነት በተጨማሪ በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍሪካ አህጉር ፕሬዚዳንት በመሆን እየሠራን እንገኛለን። የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍሪካ አህጉር ጽሕፈት ቤትም ያለው በሀገራችን ኢትዮጵያ ነው። ጽሕፈት ቤቱ ከዚህ በፊት ቡሪንዲ የነበረ ቢሆንም፤ የእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ወደ ጄኔቫ ተዘዋውሮ ነበር።

ጽሕፈት ቤቱ ወደአህጉሩ ይመለስ በሚል የተወሰነ በመሆኑ በሀገራቸው እንዲሆን አስር ሀገራት ተወዳድረው ነበር። ከእነዚህ አስር ተወዳዳሪ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ፣ ናይጄሪያ፣ ኬንያ እና ግብጽ የተለዩ ሲሆን፣ እኛ እነዚህን በምርጫው አሸንፈን ጽሕፈት ቤቱን ወደሀገራችን ማምጣት ችለናል። ኢትዮጵያ ሊያስመርጣት የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ስለነበሩ ጽሕፈት ቤቱ እኤአ በ2016 አዲስ አበባ መሆን ችሏል።

ሌላው አሜሪካ ሀገር የብሔራዊ የውቂያኖስ እና የከባቢ አየር አስተዳደር (National Oceanic and Atmospheric Administration) የሚባለው የአፍሪካ ዴስክ ባለሙያዎቻችንን የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ጭምር በመስጠት ያግዘናል። ከእነርሱ ጋር ጥሩ ግንኙነት አለን። ከኢጋድ ጋር የኢጋድ የአየር ጸባይ ትግበራ ማዕከል የኢጋድ የአየር ንብረት ትንበያ (IGAD Climate Prediction) የሚባል አለ፤ እዚያ ላይ ከፍተኛ ሚና ስንጫወት ነበር። ሌላው የአፍሪካ ሜትሮሎጂ ልማት ማዕከል (African Center of Meteorological Application for Development) ከሚባለው ጋርም ጥሩ ሥራ እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በበልግ የሚጠበቀው የአየር ሁኔታና ጸባይ እንዴት ይገለጻል? ይዞ የመጣው እድል ነው ወይስ ስጋት?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ኢትዮጵያ የምታስተናግደው ሶስት ወቅቶች አሏት። አንደኛው ክረምት ሲሆን፣ ከሰኔ እስከ መስከረም ያለውን የሚያጠቃልል ነው። ሁለተኛው በጋ ሲሆን፣ ከጥቅምት እስከ ጥር ወር ያለውን የሚይዝ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የበልግ ወቅት ሲሆን፣ ከየካቲት ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር ያለውን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ ወቅቶች እንደየአካባቢው የሚለያዩ ሲሆን፣ አንዱ ጋ ያለው የዝናብ ወቅት ክረምት ሲሆን፣ ሌላው ጋ ደግሞ በልግ ላይ ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ እነዚህ ወቅቶች ከመግባታቸው በፊት ትንበያ ይሰጣል።

የዘንድሮው የበልግ ወቅት የሚኖረውን የዝናብ መጠንና ያም የዝናብ መጠን በውሃ፣ በግብርና፣ በአደጋ መከላከል፣ በጤና ሴክተር ላይ ጭምር የሚኖረውን አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖ በተመለከተ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት መድረክ ላይ መረጃው ተሰጥቷል። እናም በዚያን ወቅት በሰጠነው ትንበያ መሠረት የበልግ ዝናብ ቀድሞ ሊገባ እንደሚችል እና ከአወጣጥ አንጻር ደግሞ ሊዘገይ እንደሚችል ጠቁመናል፤ ይህም ማለት ከክረምት ወቅትም ጋር ሊገናኝ እንደሚችል ለማመላከት ሞክረናል።

በልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚጠበቅ፤ በበልግ ወቅት ከሚጠበቀው ዝናብ የተለየ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚኖር፣ በሌሎቹም አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚሆን ትንበያ ተሰጥቷል።

ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የተገለጸው ከግብርና አንጻር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎችን አጠናክሮ መቀጠል ሲሆን፣ እንዳለፉት የበልግ ወቅቶች የዝናብ እጥረት የማይታይበት መሆኑን ለመግለጽ ተሞክሯል። ግማሽ ያለፉትን ሁለት ወራት የካቲትና መጋቢት አፈጻጸማቸውን ገምግመን የሚጠበቀውን ይፋ አድርገናል።

የሚጠበቀው መልካም አጋጣሚዎች አሉት። ይኸውም ቦረና፣ ሱማሌ እና ጉጂ አካባቢዎች ዘንድሮ እንዳለፈው ጊዜ ለተከታታይ አምስት ወቅት ያጡትን ዓይነት የዝናብ እጥረት ስለማያጋጥም ለአርብቶ አደሩ የምስራች ነው። እነርሱ የሚፈልጉት ወቅት ይህን ወቅት በመሆኑ በዚህ ወቅት ዝናብ አለ፤ ክረምት ላይ ግን የእነርሱ በጋ ነው። ስለዚህ በዚህ ጊዜ በሚያገኙት ዝናብ ውሃ መያዝ የሚያስችል ግድቦችን በመሥራት ውሃ ቢይዙ በበጋ ወቅት ላለው እንቅስቃሴያቸው አይቸገሩም። ለከብቶቻቸውም ሆነ ለመጠጥ ውሃ ያገለግላል።

በሌሎቹ አካባቢዎች በልግ የዝናብ ወቅታቸው ላልሆነና በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነባቸው አካባቢዎች ደግሞ አሁን የመኸር አሰባሰቡ ስላለቀ ዝናቡ የሚያበላሸው ሁኔታ ስለሌለ ምርትና ምርታማነት ስለሚጨምር በበጋ የሚመረተው ስንዴ ላይ የውሃ እጥረት ሳያስከትል ጥሩ ምርት እንዲኖር ያስችላል።

ሌላው ከውሃ አስተዳደር አንጻር የኤሌክትሪክ መቆራረጥ እንዳይኖር ያደርጋል። በዚህ ምክንያት ምናልባት የመስመሮች መቀያየር በከተሞች አካባቢ ካልሆነ በስተቀር በውሃ እጥረት የሚመጣ የኤሌክትሪክ ኃይል በፈረቃ እንዲሆን የሚያስደርግ ነገር አይኖርም።

ከጉዳት አንጻር ከባድ ዝናብ የሚጠበቅ ስለሆነ የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎችን እንዲሁም በልግ በማይጠቀሙ አካባቢዎችም የጎርፍ ክስተት ሊያጋጥም ይችላል። ይህን ጉዳት ለመቀነስ ከአሰፋፈር አንጻር ለምሳሌ ወንዞች ዳርቻ መስፈር የመሳሰሉት ላይ ጥንቃቄ ሁልጊዜ ማድረግ ያስፈልጋል። ሁለተኛው ደግሞ በከተሞች አካባቢ የውሃ ማስወገጃ ቦዮች ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ስለዚህ በችግሩና በመልካም አጋጣሚ መካከል ያለውን ሁኔታ ሚዛን አስጠብቆ መሄድ ጠቃሚ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ፈጠነ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## በጉንጉን ስብጥርጥር

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

እንቆቅልህ! ብትሉኝ፤ እኔም ምናውቅ... ብል፤ የእንቆቅልሻችሁን ምላሽ ግን ባውቅም አልነግራችሁ! ምክንያቱም "ሀገር ስጠኝ" እስክትሉኝ ጠብቄ ሀገር ልሰጣችሁ እፈልጋለሁና። ታዲያ ግን የምሰጣችሁ ማንን እንደሆነ ከገመታችሁ ዘንድ ልንገራችሁ... ያቺን የጉንጉን መሶብ፤ ማጀቴን ልሰጣችሁ ወስኛለሁ።

ምን አለ ከማጀቴ? ካላችሁኝ፤ በእግዜር እጆች በተፈጥሮ ቀለማት በተነከረው የማጀቴ እንብርት ላይ፤ ከጥበብ ብዕር በቆመ ካስማ፤ በምናብ ከተሰናሰነ ወጋግራ፤ በከዋክብትና በብርሃን ጸዳል የቆመች አንዲት ዓለም ተገኝታለች። እሷም "ጉንጉን" ትባላለች፤ እዚያ...ጉንጉን አበባ፤ ጉንጉን ሕይወት፤ ጉንጉን ማንነት፤ የተጎነጎኑ የምናቡ ዓለም የሕይወት ገጸ በረከቶች አሉና ይዘን እንመለሳለን።

ለጉብኝቱ አንዳችም ሃሳብ እንዳይገባችሁ፤ እኔ አለሁና ከጉንጉን ጥበበ ሠሪ፤ ከምናብ ጌታው መድረሻ ማዳረሻውን እቀበላለሁ። መሄዱን ለመረጣችሁም መንገዱ እሩቅ አይደለም። ከመንደርደሪያችሁ አሊያም ከመደብር ጎራ ብላችሁ "ጉንጉን" የምትለዋን መጽሐፍ ያዙ። እኔም፤ እንዲያ ብዬ አልተዋችሁምና በሸንተረራማው ስብጥርጥር፤ ግማሽ መንገዱን ከ"ጉንጉን" ስብጥሮች ጋር ልሸኛችሁ እመርጣለሁ።

ጉንጉን በ1982ዓ.ም ነበር ተወልዶ ለንባብ የበቃው። የመጽሐፉ መሠረት ሲጣል እንዲያው እንደዋዛ ከትንሽዬ የብዕር ጠብታ ነበር። በወቅቱ የነበሩት ደራሲያን የማህበራዊ ሕይወት የደረጀ ነበርና አንጋፋዎቹ ሰበብ ብለው ሻይና ቡናቸውን ፉት እያሉ ስለመጻሕፍት ዓለም የሚጨዋወቱባት የሚያወጉባት ክበብ ቢጤ ነበረቻቸው። ከዚህ ስፍራ ሲገናኙ ሁሉም በተቻላቸው አቅም የጥበብ አቁማዳቸውን ሞልተው፤ ብጣሽ ወረቀትም ብትሆን ከኪሳቸው ሸጎጥ አድርገው ነውና ከዚሁ ተነስታ የተመነደገች ነበረች።

ደራሲው ኃይለመለኮት መዋዕል በጉንጉን ዓለም መስታወት ፊት ቆሞ አሻግሮ እሩቁን ማየት ጀመረ። የተባ ብዕሩን ዐሻራ ይዘው የወጡ መጻሕፍቶቹ ብዙ ቢሆንም "ጉንጉን" የተሰኘችው የዛሬው መጽሐፉችን ግን ከደራሲው ለአንባቢያንና ለጥበብ የተበረከተች ጉንጉን አበባ ናት። መስጠት ብቻም ሳይሆን ጉንጉን ምስጋናና ክብርም የተቀዳጀባትና የተቸረባት ናት። ምናልባትም የኃይለመለኮትን ልክ ይዛ የተከሰተችም ጭምር ናት። የዚህች መጽሐፍ የታሪክ ጥንስስ ከማጀቴ ምድር ላይ ነው።

ወደ ማጀቴ እናዝግም። ከማጀቴ ገበያ ወጥተን እህልኑም...ምናምኑን እንሸማምት፤ ወደ ጃራ ወንዝ ወርደን ውሃ እንቅዳ፤ እየዋኘን በልጅነት ትዝታችን እንሳፈፍ፤ ከምንወዳት የማጀቴ ጉብል ጋር ከወንዙ ዳር ሆነን ፍቅር እንስራ...የፍቅርን ቄጤማ ቆርጠን ከድልድዩ ስር በመጎዝጎዝ በፍቅር እነሆልል!፤ ከጎረቤትም ብቅ ብለን ከነ እልፍ ይከንዱ ቤት ቡናውን ፉት ብለን ከቀኛዝማች በላይነህ ክንዴ ጋርም በጨዋታ እናውጋ።

አንቱ በእርሶ መጀን ያሸማግሉን እንበላቸው፤ ከእርሳቸው ቤት ያለው አሽከራቸው እርም አይቀሬ... ደግሞ ያ ማነው የሚሉት... አፈሳ፤ የፈሪ ዱላ መሳይ የፍቅር ጌታውን ምንዳን ቁምስቅሉን እያሳየ አላስቆም አላስቀምጥ ብሏልና ለእርሱስ መካሪ ከወዴት እናገኝለት ይሆን...ብቻ ግን በማጀቴ አፈር ለሁሉም መላ መላውን አናጣምና ወደዚያው እናምራ። ለስንቁም ቢሆን አንዳችም ሃሳብ አይግባን የማጀቴ ሕዝብ በክብር ተቀብሎና እግር አጥቦ እያንከባከበ ያሰነብተናል።

በማጀቴ ቆይታችን የማንመለከተው ጉድ የለም። አመለኛውን ከነአመሉ፤ ጻዲቁን ከነጽድቁ፤ አሸርጋጁን ከነሸርግድ ማንነቱ፤ ሃይማኖተኛውንም እብሪተኛውንም፤ ሕፃን አዛውንት፤ ቆንጆ ጉብል ኮረዳ፤ ለዓይንና ለልባችን አዲስ የሆነ የፍቅር ቄጤማ፤ በአጠቃላይ ግን በ"ጉንጉን" ዓለም ውስጥ ከምንም በላይ ያማሩና ውብ የሆነ የማህበረሰብ እሴቶቻችንን ከነ ነብሳቸው በአካል የቆሙ ያህል ሆነው እናያቸዋለን።

በኃይለመለኮት ምናብ ውስጥ የተሳሉት ገጸ ባህሪያት በመጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምናባዊ ፈጠራዎች ሳይሆኑ ከእኛው መንደር ውስጥ ያሉ መስለው ይታዩናል። አስቀድሜ ወደ ማጀቴ እንሂድ ማለቴ፤ የመጽሐፉን ገጾች ባገላበጥን ቁጥር እራሳችንን እንደ አንድ የማጀቴ ነዋሪ መቁጠራችን አይቀርም በማለት ነው።

ምናልባትም ደግሞ እራሳችንን እንደ አንደኛው ገጸ ሰብ ቆጥረን ወዳጁ ወዳጃችን፤ ጠላቱም ጠላታችን ሆኖ አብረን እላይ ታች እንል ይሆናል። ታዲያ ግን ለማንኛውም፤ እንደ ዶሮ ጫር ጫር እያደረኩ ከነዋሪው መሃከል ጥቂቱን ገጸ ባህሪያት በትንሽ በትንሹ ላስተዋውቃችሁና ሸኘ ቤት አያደርስምና... ዝምድናና ወዳጅነቱን ለማጠንከር ከፈለጋችሁ ቀሪውን እናንተው ተገናኝታችሁ ጨርሱት።

ይገርማችኋል ምንዳና ልክየለሽ እንዴት ያሉ ባልና ሚስት መሰሏችሁ... አቤት ፍቅር!፤ አይ መውደድና መዋደድ አንዱ ለአንዱ ያለው መተዛዘን..ጣዝማውን የፍቅር ማር እየቆረጡ ሲጎራረሱማ፤ አንተን ባደረገኝ ምንዳ፤ አንቺን በሆንኩ ልኬ ያስብላሉ። ይህ ፍቅርማ ከአንዱ ስፍራ በቀር ከወዴትም አይገኝምና መምህራቸው ከወዲያው እንደሆነ ያስጠረጥራል። የጉንጉኖቹ ምንዳና ልኬለሽ የፍቅር እስከ መቃብሮቹ በዛብህና ሰብለ ወንጌል አንዳች ግንኙነት ሳይኖራቸው እንደማይቀር ጠረጠርኩ። ይህን ፍቅር ምንዳ ከበዛብህ፤ ልክየለሽ ከሰብለ ወንጌል እግር ስር ቁጭ ብለው የተማሩት ይመስለኛል። አሊያማ እጅን በአፍ የሚያስጭን የእነርሱን ፍቅር መሳይ የታደለ ሌላ ገጸ ባህርይ ለማግኘት የሚቻል አይመስለኝም።

ታዲያ ምን ያደርጋል፤ የፍቅር አበባ ባለበት የፍቅር መቀስ፤ መለያየት የሚሉት የፍቅር ጥቀርሻ አይጠፋምና ...የኔ ነገር... በፍቅራቸው መዓዛ ነሁልዬ ሌሎቹን እንዳልዘነጋቸው...የቀዬው ጌታ፤ ቀኛዝማች በላይነህ ክንዴም የዋዛ ሰው እንዳይመስሏችሁ የሰማንያ ሚስታቸውን የእልፍይከንዱን ፍቅር በጭልፋ፤ የቅምጣቸውን የወይዘሮ ደጅይጥኑን ደግሞ በማንኪያ የሚዝቁ ብቻም አይደሉም።

አንዳንዴ በሹኪያም ይዳዳቸውና ወደ አገልጋያቸው ላቀች ዓይነ ስሜታቸውን ያዞራሉ። በጠበቅናቸውም ባልጠበቅናቸውም ቦታ ድንገት የምናገኛቸው የሁለት ዓለም ሰው ናቸው። ቸርነት እንደ ስሙ ቸር ነው። የምንዳ የልብ ወዳጅ ብቻም ሳይሆን አንዳንዴማ ልቡም ጭምር ነው። ጓደኝነትና የልብ ወዳጅነት ሲሰምር ልክ እንደ ሁለቱ ያለውን እንዲሰጣችሁ ተመኙ። ምንም የማይወጣለት ንፉስም ሆነ ዝንብ የማይገባበት ጸአዳ ወዳጅነት ነው።

አለ ደግሞ እንደ አፈሳ ዓይነቱ ፍጹም ጠላት፤ ቅናት እያንጨረጨረው የተንኮል ጅራፉን በፍቅር ዜማ መሃል ድንገት ያስጮሃል። የተንኮሉን ያህል አብዝቶ የተከናነበው ፈሪነቱ ደግሞ አይጣል አያድርስ የሚያስብል ነው። የፈሪ ዱላ ሁሌም የሚመታ ስለሚመስለው ከአንድ አንድ ሳልቀደም ልቅደም በማለት አድብቶ በአሳቻው ሰዓት ከማጅራት ላይ ይወርዳልና በዚህም ምክንያት እርሱ የጠላው ሁሉ ጠላቱ ይመስለዋል። ደጉንና ምስኪኑን ምንዳዬን ዋነኛው ጠላቱ አድርጎ በዚህም በዚያም ሲያዋክበው አንጀት የሚያሳርር ነው።

ብቻ ግን የደራሲው ምናቦች ግብራቸው በሰማይና በምድር መሃከል እንደ ሰማይና እንደ ምድር፤ እንደ መልዓክና እንደ ሰይጣን ያሉ ናቸው። ወደን እስከ ጥግ የምንወዳቸው፤ ጠልተንም እስከ ጥልቁ የምንጠላቸው ሆነው ይገኛሉ። ታዲያ በእነዚህ መሀከል የሚፈጠረው ዓለም እንዴት ያለ ጣፋጭ መሰላችሁ፤ ስሜት የሚያስቆረጥም ነው።

በ"ጉንጉን" ውስጥ የምንመለከተው የደራሲው ልዩ ችሎታና በገጸ ባህሪያቱ ውስጥ የተሰካኩት የሴራ ውቅሮች፤ እጅግ የምንደነቅበት ሌላው እይታ ነው። ብዙውን ጊዜ፤ ቀኛዝማች በላይነህና ባለቤታቸው እልፍይከንዱ በመሃከላቸው የሚፈጠር ሙግትና የውስጥ ግጭት አለ። ይህን አለመግባባት በቃላት አሳምሮ ማስቀመጥ የሚቻል ቢሆንም፤ ደራሲው ግን




ሌላ የተለየ እይታን ለመፍጠር ታትሮበታል።

በዚህ መሃል ከቃላቶቻቸው የተለየውን ውስጣዊ የስሜት ነጸብራቅ፤ በቃላት ልንረዳው ከምንችለው በላይ በስዕላዊ እንቅስቃሴና በውስጣዊ ስሜታቸው ይነግረናል። ቃላትን በመጠቀም ስሜትን ከመግለጽ ይልቅ ስሜትን በመጠቀም ያልተጻፉ ቃላትን እንድናነብ ያደርገናል። እልፍ ይከንዱ በትንሽ ትልቁ አብዝተው የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት የሚማጸኑና ስለት የሚወዱ ሴት ናቸው። በታቦቱ ካላቸው የገዘፈ እምነት የተነሳ መልካምና ደጉን ቀርቶ ለመንቀል የፈለጉትን ሰው እንዲነቅልላቸው ቢማጸኑት እንኳ እንደሚያደርግላቸው ያምናሉ።

ይህን ብታደርግልኝ፤ ዣንጥልና እጣን ከርቤውን...ስለቱን አስገባልሃለሁ ብለው ተማጽነው፤ ነገር አልሆን ስለቱ አልሰምር ያላቸው ጊዜ አፈንግጠው ጊዮርጊስ አልሰማኝም በማለት ወደ ጠንቋይ መንደር ይዘልቃሉ። ባለቤታቸው ቀኛዝማች ደግሞ የኔ የሚሉትና የቅርባቸው የሆነው መልዓክ ቅዱስ ሚካኤል ነው ይላሉ። ሁለቱም በየራሳቸው መልዓኮች ያላቸው የከረረ እምነት፤ የኔው የኔ ብቻ ነው ወደሚመስል ስሜቶች ሲገቡ እንመለከታለን።

አውጥተው በቃላት ባይተነፍሱትም፤ በውስጣቸው አንዱን መልዓክ ከሌላው ማበላለጥና የኔው ነው የሚበልጠው ብሎ የማሰብን አዝማሚያቸውን ያለምን የቃላት ገለጻ እንዲሁ ውስጣቸውን ለመረዳት ስንችል፤ እንዴት ያለው ግሩም የስሜት መነጽር ነው፤ በማለት ደራሲውን ለማድነቅ አፍታም የምንዘገይ አይመስለኝም። "እርም አይቀሬ" የተባለውን የቀኛዝማች የበላይነህ አሽከር፤ ከስሙ ጀምሮ ያለውን ማንነቱን ለመረዳት ሌላ የተለየ መነጽር የሚሻ ነው።

አንድ ቀን፤ እልፍይከንዱ እንደ ልማዳቸው ታቦቱን ተማጽነው፤ ነገሩ አልሆን ቢላቸው ጊዜ ጊዮርጊስ ቀድሞ አልደረሰልኝም በማለት ወደ ጨፍሮቢቷ ጠንቋይ ዘንድ ሄዱ። "...የጠጡትን ስኒ ቡና አተላ በቀስታ እያንጋለሉ ካጠነፈፉ በኋላ፤ ቀሪው አተላ ረግቶ የራሱን የመፍሰሻ ሸንተረራማ ስብጥርጥር ሥዕል መሥራቱን እንዳዩ..."

መጽሐፍ ውስጥ የምናገኛቸው የገጸ ባህሪያቱ ድርጊቶች፤ አንዳንዴም ደራሲው ምን ሲል አሰበው የሚያስብሉን ናቸው። በተመስጦ ውስጥ ሆነን ገጽ ለገጽ የቃላቱን ፍኖት ተከትለን ስንሄድ፤ ድንገት ንባባችንን ገታ አድርገን ነገሩን በአዕምሯችን ለማሰላሰል እንገደዳለን። አንድ ደራሲ ያን ያህል ተጨንቆና ተጠቦ በዚያ መልኩ ይገልጸዋል ብለን የማንጠብቀውን፤ በእውን እንጂ በምናብ ፈጠራ ውስጥ ልናገኘው የማንችለውን ነገር ያሳየናል።

ጥቃቅንና ከአንድ ጊዜ በላይ ደግመን ልናያቸው የማንችላቸው፤ ነገር ግን እኛ እንደዋዛ ተመልክተን ያለፍነውና አዕምሯችን ግን ከማህደሩ አስፍሮት በሆነ ጊዜ በሆነ አጋጣሚ ትዝ የሚሉን ግላዊ ክስተቶች የበዙበት ነው። መጽሐፉ በአንድ አካባቢ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ልቅም አድርጎ አስቀምጦታል። እንደ ምናብ ቁብ የማንሰጣቸው፤ እንደ እውነት ግን ቅልብጭ ያሉ እውነታዎች ታጭቀውበታል።

አልፎም ደግሞ ሰው እንደመሆናችን በሰዋዊ ተፈጥሯችን በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ተሰንገው ሳሉ፤ ነገር ግን ሁላችንም ውስጥ ውስጡን ስናብሰለስላቸው በግልጽ አውጥተን እንዲህ ነው የማንላቸውን ጉዳዮችንም፤ ባህልና ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። የደራሲው ዓይንና የምናቡ ስፋት የተለየ ስለመሆኑ፤ እኚህ በድንገት የምናገኛቸው አዳዲስ እውነታዎች ይነግሩናል። የታሪክና የቦታ፤ የገጸ ባህሪያቱና የድርጊት ስብጥሮቹ ከቃላቱ ጋር የተሰናሰኑበት ዘዬ ማራኪ የጽጌረዳ ጉንጉን አኑሮበታል።

በልቦለድ የምናብ ዓለም ውስጥ እጅግ ወሳኝና የደራሲው የምናብ ጥልቀት የሚፈተንበት አንደኛው ነገር የቦታና ቁስ አካላትን ስዕል መፍጠር ላይ ነው። ገጸ ባህሪያቱ በራሳቸው ቃላትን በመጠቀም ስሜትና ባህሪያቸውን ሊነግሩን ይችላሉ። ግኡዝ አካላትን በተፈጥሮ ልኬት መልክና አንዳንዴም ሰውኛ ባህሪን እያላበሱ እነርሱን ነጋሪና ተናጋሪ ማድረግ የተለየ ጥበባዊ ክህሎትን የሚጠይቅ ነው።

ከገጸ ባህሪያቱ፤ እንቅስቃሴና የቃላት ምልልስ ይልቅ ያሉበትን አካባቢ፤ መልክዓ ምድራዊ ገጽታውን ምስል ከሳችና መሳጭ ማድረግ ይበልጥ የሚስብና የአንባቢውንም ምናባዊ አብሮነት ሳይቋረጥና ሳይቀዘቅዝ እንዲቀጥል ያደርገዋል። በዚህ ሚዛን ውስጥ "ጉንጉን" አንዳች ማግኔታዊ ስበት ያለው ይሆንና ገጸ ባህሪያቱን ረስተን በቦታው የተገኘነው እኛ እንደሆን ይሰማናል። የማህበረሰባችንን ቀደምት ልምዶችንና ባህላዊ የማንነት እሴቶቻችንን መልክ ይዞና እንደ ጉንጉን አበባው ስጦታ እንካችሁ ሲል ይሰማናል። ኢትዮጵያዊነት አፍ አውጥቶ ሲናገር እንመለከታለን። ወይዘሮ ደጅይጥኑ ከአቦ ፀበል መልስ በሼህ መሐመድ መቃብር በኩል ሲያልፉ፤

**"በአንቱ ከራማ፣ በአንቱ መጀን፤**
**አባቴ የኔ አድባር የዕለት ጉርሴን፤**
**የዓመት ልብሴን አትንፈጉኝ፤"**

በማለት በግጥማዊ የተማጽኖ ዜማ፤ ውስጥን የሚፈነቅል ኢትዮጵያዊ ማንነታችን በልባችን እንደ ቀስተ ደመና ያለ መስመር ሰርቶ ሲያልፍ ይሰማናል። ከቀብሩ ስፍራ ደርሰው መጀን ማለታቸው፤ እንደዋዛ ሲያልፉ ብቻ ሳይሆን ከአቦ ፀበል፤ ከመድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ፀሎት አድርሰው ሲለን፤ ለነገሩ ክብደት ለመስጠት ብቻም ሳይሆን፤ ደራሲው እዚች ጋር ለማስቀመጥ የፈለገው ጉንጉንም መኖሩ ነው።

አይ ክፉ ቀን! ያ የፍቅር መሶብ፤ የመልካምነት አገልግል ምንዳ ከጠላቱ እጅ ወደቀ። በጥይት ተመቶ ወደቀ። ይሄኔ ልክየለሽ ምን ይውጣት ነጠላዋን ከወገቧ ላይ አድርጋ እሪ! እያለች እንባዋን እያዘራችው ነው። ምስኪኖቹ ሕፃናት ልጆች፤ ከደጁ ላይ ኩርምት ብለው፤ ዓይኖቻቸውን ሲያንከራትቱ አንጀትን ይበላሉ።

ጉንጉን ከወዲያ ወዲህ እየጎነጎነ የሚያሳየንና የሚሰጠን በምናባዊ ቀለማት የተቀለመው የማህበረሰባዊ የጋቢ ጥለት ውስጥ የማናገኘው እኛነትና እኔነት የለም። ከድውሩ እስከ ጥለቱ መቋጫ ድረስ ባለው ሂደት፤ እንደ ባለሙያው የምንሠራውም፤ እንደ ጋቢውም የምንሠራው እኛው ሆነን እንገኛለን።

"ጉንጉን" በራሱ ዛቢያ፤ በሚያደርገው በምናባዊ እሽክርክሪቱ እየከሰተ ባሳየን ድንቅ ዓለምና ድንቅ ታሪኩ ብቻም ሳይሆን፤ እንደ መጻሕፍት ዓለም ከዋክብቶቻችንም አብረቅራቂው የኦሪዮን ኮከብ ነው። በጣት ቆጥረን ከምንጠቅሳቸው መጽሐፍቶቻችን መሃከል "ጉንጉን" ስለመኖሩ ማናችንንም የሚያወላዳ አይደለም። እናም ስብጥርጥሩን የማጀቴን መንገድ ተከትላችሁ ሂዱ ይህቺን ማጀቴ፤ ያንንም ጉንጉን ያዙ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚተጋው ‹‹ኢንዳን››

እዮሩስ ተስፋዬ

የቀድሞ መጠሪያው ‹‹ሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር›› እና በዓለም የሠራተኞች ድርጅት (ILO) አማካኝነት ‹‹ዲስኤቢሊቲ ፎረም›› በሚል ስያሜ ነበር የተቋቋመው፡፡ የአሁኑ ስያሜው ‹‹ኢትዮጵያን ናሽናል ዲስኤቢሊቲ አክሽን ኔትዎርክ››(ኢንዳን) ይባላል፡፡ አቶ ዓለሙ ኃይሌ ደግሞ የተቋሙ ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡

‹‹ኢትዮጵያውያን አብሮ የመብላት ችግር የለብንም። በጋራ የመሥራቱ ነገራችን ግን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው።›› የሚሉት አቶ ዓለሙ፤ ከዚህ ሃሳብ በመነሳትና በጋራ መሥራት እንደሚቻል በማመን በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶች በተናጠል ከሚሠሩ ይልቅ እነርሱን አቅፎና ደግፎ ችግራቸውን በጋራ የሚያሰሙበት ድርጅት የዛሬ 20 ዓመት እንደተመሰረተ ያስታውሳሉ፡፡

በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የተለያዩ ሥራዎችን የሚሠሩ 34 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የ‹‹ኢንዳን›› አባል እንደሆኑ የሚገልጹት አቶ ዓለሙ፣ ከአባላቱ መካከል ሁለቱ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ አገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለፃ፣ የአንድ ሰው ድምጽ እና የ34 ሰዎች ድምጽ አንድ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህም ድርጅቱ በዋናነት የሚሠራው በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ላይ የሚሠሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ድምጻቸውን በጋራ እንዲያሰሙ ማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም ከመንግሥት ጋር በጋራ በመሆን የሚወጡት ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ የሕግ ማዕቀፎች እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ትኩረት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ በምን መልኩ ታይቷል በማለትም ከመንግሥት ጋር በጋራ ይሠራል፡፡ ከዚህ ባለፈ ለአባላቶቹ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት እና ከሚያገኘው ድጋፍ አባላቶቹን መልሶ መገደፍ አንዱ ተግባሩ ነው፡፡

‹‹ኢንዳን›› የተለያዩ አባላቶች ያሉት ሲሆን አባላቶቹ ከተቋቋሙለት ዓላማ በመነሳት እና የሚሠሩትን በጎ ሥራ መሠረት አድርጎ የተለያዩ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጥረት ያደርጋል፡፡ ለአብነት የዳንቴል ውጤቶች፣ ስጋጃ፣ እና መሰል ምርቶችን በመሥራት ጥረት ለሚያደርጉ ድርጅቶች ምርቶቻቸው ገዢ እንዲያገኝ ያበረታታል፡፡ በተለያዩ ባዛሮች ላይ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮም ከፋይናንስ ተቋማት እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመወያየት አካል ጉዳተኞች ማምረት እና መሥራት እንደሚችሉ እነርሱም ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ግንዛቤ የመስጠት ሥራዎችን እንደሚሠራ አቶ ዓለሙ ያስረዳሉ፡፡

አቶ ዓለሙ እንደሚገልጹት፣ ኢንዳን የተለያዩ አባላቶች አሉት፡፡ በኢትዮጵያ ጥቂት ከሚባሉ ኦቲዝም ላይ ከሚሠሩ ድርጅቶች መካከል ጆይ የኦቲዝም ማዕከል፣ ነህምያ የኦቲዝም ማዕከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የአእምሮ እድገት ውስነንት ላይ ከሚሠሩት መካከል መካነ ኢየሱስ፣ ፍቅር ኢትዮጵያ የአእምሮ እድገት ውስንነት ብሔራዊ ማህበር ፣ቁጥራቸው በዛ ያሉ ዓይነ ሥውራን ላይ የሚሠሩ ማሕበራት፣ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማሕበር፣ የአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማሕበር፣ የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ብሔራዊ ማሕበር እና ሌሎቹም ካሉት 34 አባላት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

ቆየት ካሉ ጥናቶች በመነሳት በአገራችን 20 ሚሊዮን አካል ጉዳተኞች መኖራቸው ይገለጻል፡፡ በአሁን ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ቁጥሩ ከፍ ቢል እንጂ ሊቀንስ እንደማይችል መገመት አያዳግትም፡፡ አቶ ዓለሙም የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ በፋይናንስ ተቋማት በኩል ብድርም ይሁን ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይገባል ይላሉ፡፡ አካል ጉዳተኞች የሚስተናገዱበት ልዩ መስኮቶች ቢዘጋጁም ተቋማቱ የበለጠ ተመራጭ እና ብዙ ተገልጋይ እንዲኖራቸው ያግዛል ይላሉ፡፡

በሁሉም ክፍለ ከተማ ደረጃ ባዛሮች ይዘጋጃሉ፣ ነገር ግን የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ የለም ማለት ይቻላል ያሉት አቶ ዓለሙ፣ መንግሥት በሚያዘጋጃቸውም ሆነ ፍቃድ በሚሰጥባቸው ባዛሮች ላይ ተሳትፏቸው እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ሥራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ቢደረግ ተጠቃሚነታቸውን ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ያምናሉ፡፡

‹‹የተጠቃለለ የአካል ጉዳተኞች ሕግ›› ጸድቆ ወደ ተግባር ቢገባ አካል ጉዳተኞች ስለሚገጥማቸው ችግር ግንዛቤ ከመስጠት ባሻገር ሕጉ አስገዳጅ እንደመሆኑ ብዙ ችግሮችን ሊፈታ እንደሚችልም ይናገራሉ፡፡ አያይዘውም አካል ጉዳተኝነት እና ሞት መምጫቸው አይታወቅና ሁሉ ሰው ለራሱ ሲል የድርሻውን በጎ ነገር ማበርከት እንዳለበት ይመክራሉ፡፡

ድርጅቱ በ20 ዓመታት ውስጥ በርካታ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡፡ በተለያዩ አገራት ላይ ባሉ ጦርነቶች፣ የኑሮ ውድነት እና በሌሎች ችግሮች ምክንያት በለጋሽ አገራትም ሆነ ድርጅቶች በኩል እጅም ፍላጎትም እያጠራቸው እንደሆነ የሚገልጹት አቶ ዓለሙ፣ ድርጅቱ በፊት ከሚያገኘው ድጋፍ አንፃር ከፍተኛ የድጋፍ መቀዛቀዝ ታይቷል ይላሉ፡፡ ሌላው ችግር የኢንዳን አባል የሆኑ ድርጅቶች የድጋፍ እጥረት ስላለባቸው ሊዘጉ የደረሱ ድርጅቶች ቢኖሩም ለእነርሱ ለመድረስ አለመቻላቸውን ከገጠማቸው ተግዳሮት አንዱ እንደሆነ ያነሳሉ፡፡ በተጨማሪም በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ባለው የጸጥታ ችግር እንደልብ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት አለመቻልም ሌላኛው ፈተና ነው፡፡ ከሁሉም ከሁሉም ግን ቀጣይነት ያለው ፈንድ አለመገኘቱ ድርጅቱን እየፈተነው ያለ ነገር መሆኑን በማንሳት የሚመለከተው አካል ድጋፉን እንዲያደርግ ይጠይቃሉ፡፡




ኢንዳን ከተቋቋመለት ዓላማ በመነሳት በቀጣይ አባል ድርጅቶቹ ያለምንም ችግር በጎ ሥራቸውን ከውነው ለብዙዎች ሲደርሱ ማየት ይፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በሁሉም ዘርፍ አካል ጉዳተኞች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተለይም የሚመለከተው አካል ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት ኢራን ላይ ማዕቀብ ለመጣል ዝግጅት ጀመሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩናይትድ ስቴትስ እና የአውሮፓ ኅብረት፤ እስራኤል ላይ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ ኢራን ላይ ተጨማሪ ማዕቀብ ለመጣል እየተሰናዱ ነው።

የአሜሪካ ግምጃ ቤት ኃላፊ ጃኔት የለን "በሚቀጥሉት ቀናት" ርምጃ እንወስዳለን ሲሉ የአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊስ ኃላፊ ጆሴፍ ቦሬል ደግሞ ኅብረቱ ማዕቅብ ለመጣል እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

እስራኤል አጋሮቿ የኢራን የሚሳዔል ፕሮግራም ላይ ማዕቀብ እንዲጥሉ ጠይቃለች። የተባበሩት መንግሥታት የኢራን የሚሳዔል ፕሮግራም ላይ የጣለው ማዕቀብ ባለፈው ጥቅምት ጊዜው አብቅቷል።

እነዚህ ማዕቀቦች የሚጣሉት የኢራንን የኒውክሌር ፕሮግራም ለመግታት ነው የሚሉ ሃሳቦች ከፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ይሰማሉ።

አሜሪካ፣ የአውሮፓ ኅብረት እና ዩናይትድ ኪንግደምን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ኢራን ላይ የተለያዩ ማዕቀቦች ከዚህ ቀደም መጣላቸው አይዘነጋም።

የእስራኤል ጦር ሠራዊት ኤታማዦር ሹም ሌተናንት ጄኔራል ሄርዚ ሀሌቪ ባለፈው ሰኞ በሰጡት አስተያየት ኢራን ያደረሰችው ጥቃት ምላሽ ሳያገኝ አያልፍም የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር።

ኢራን ባለፈው ቅዳሜ ለመጀመሪያ ጊዜ እስራኤል ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ባደረሰችበት ወቅት 300 ሚሳዔሎችና ድሮኖች ከራሷ ክልል፣ ከኢራቅ፣ ሶሪያ እና የመን አስወንጭፋለች። አብዛኞዎቹ ሚሳዔሎች እና ድሮኖች በእስራኤል እና አጋሮቿ ዒላማቸውን ሳይመቱ እንዲከሽፉ ተደርገዋል።

ቴህራን እንዳለችው ጥቃቱን የሰነዘረችው እስራኤል፤ ሶሪያ በሚገኘው ቆንስላዋ ላይ ጥቃት አድርሳ 13 ሰዎችን ለገደለችበት ጥቃት አፀፋውን ለመመለስ ነው።



እስራኤል ለደረሰባት ጥቃት እስካሁን ቀጥተኛ ምላሽ አልሰጠችም። በምትኩ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ኢራንን ለማሸመድመድ እየሠራች ትገኛለች። እስራኤል 30 የሚሆኑ አጋር ሀገሮች የኢራን የሚሳዔል ፕሮግራም ላይ ማዕቀብ እንዲጥሉ ጠይቃለች።

አልፎም እስላማዊ አብዮታዊ ዘብ (ኢስላሚክ ሪቮሎሺናሪ ጋርድ ኮር) የተባለው የኢራን ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ኃይል ሽብርተኛ ተብሎ እንዲፈረጅ ጠይቃለች። አሜሪካ ከዚህ ቀደም ቡድኑን ሽብርተኛ ብትልም ዩኬ ይህን ከማድረግ ተቆጥባለች።

ማክሰኞ ዕለት ንግግር ያደረጉት የአሜሪካ ግምጃ ቤት ሚኒስትር የለን "በሚቀጥሉት ቀናት ኢራን ላይ ማዕቀብ እንደምንጥል ይጠበቃል" ብለዋል።

ሚኒስትሯ አክለው ኢራን ወደ ውጭ የምትልከው ነዳጅ "ምናልባት የምናየው ይሆናል" ካሉ በኋላ "ኢራንም አሁንም በግልፅ ነዳጅ እየሸጠች ነው፤ ስለዚህ ጉዳይ የምናደርገው ነገር ይኖራል" ሲሉ ማዕቀቡ ምን ላይ እንደሚያተኩር ጠቁመዋል።

የለን፤ ኢራን ከሀገር ውጭ ያሉ ቡድኖችን በገንዘብ እንዳትደጉም እንዲሁም ሩሲያ ዩክሬን ላይ ያወጀችውን ጦርነት እንዳትደግፍ ለማድረግ የገንዘብ ዕቀባ መደረጉን አውስተዋል።

500 ሰዎች እና ኩባንያዎች በአሜሪካ ማዕቀብ እንደተጣለባቸው ይታወቃል። አሜሪካ ኢራን ላይ በጣለችው ማዕቀብ መሠረት ሁለቱ ሀገራት ምንም ዓይነት ንግድ አያከናውኑም።

የአሜሪካው ብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ ጄክ ሱሊቫን ሀገራቸው ልትጥል ያሰበችው አዲስ ማዕቀብ የኢራንን "የሚሳዔል እና ድሮን ፕሮግራም" እንዲሁም አብዮታዊውን ዘብ እና መከላከያ ሚኒስትሩን የሚመለከት ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

የአውሮፓ ሕብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊስ ኃላፊው ቦሬል ደግሞ አንዳንድ የሕብረቱ ሀገራት ኢራን ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ጠይቀዋል ብለዋል።

ቦሬል አክለው የሀገራቱ ጥያቄ ወደ ሕብረቱ ዲፕሎማሲ አገልግሎት ተልኮ "አስፈላጊው ሥራ" ተጀምሯል ብለዋል። የዓለም ሀገራት በመካከለኛው ምሥራቅ ያለው አለመረጋጋት የበለጠ እንዳይስፋፋ ኢራን ላይ ማዕቀብ መጣል አስፈላጊ ነው ይላሉ።

ለእስራኤል ያላቸው ድጋፍ "ከብረት የጠነከረ" እንደሆነ የተናገሩት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እስራኤል ድል አውጃ "ማሸነፏን እንድትቀበል" አሳስበዋል።

የዩኬው ጠቅላይ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ ደግሞ ከእስራኤሉ አቻቸው ኔታኒያሁ ጋር ማክሰኞ ምሽት ባደረጉት የስልክ ልውውጥ እስራኤል ምላሽ ለመስጠት በሚል በቀጣናው የበለጠ አለመረጋጋት እንዳትፈጥር አስጠንቅቀዋል። ኢራን፤ እስራኤል ምላሽ እስካልሰጠች ድረስ ሁኔታው "ተቋጭቷል" ብላለች።

የኢራኑ ፕሬዚዳንት ኢብራሂም ራይሲ "ማንኛውም የኢራንን ፍላጎት ሊነካ የሚችል ነገር ላይ የሚደርስ ጥቃት አፀፋው በጣም የከፋና ስቃይ የበዛበት ሊሆን ይችላል" ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

የኢራን አጋር የሆነችው ሩሲያም በቀጣናው መረጋጋት እንዲመጣ የጠየቀች ሲሆን፤ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከፕሬዚዳንት ራይሲ ጋር ባደረጉት የስልክ ልውውጥ ሁኔታው ቀዝቀዝ እንዲል መጠየቃቸውን ክሬምሊን አስታውቋል።

# ጎሜ

# አበባዎቹ በኢትዮጵያዊ ማንነት ይታነጹ

**እፀገነት አክሊሉ**

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም በአንድ የጋራ መኖሪያ መንደር ላይ በጉርብትና የሚኖሩ ናቸው። እድለኞች ሆነው ሁለቱም የቤት ባለቤት በመሆናቸው ጉርብትናቸውም ዘለቅ ያለ ጊዜን አስቆጥሯል። ይህ ረዘም ያለ የጉርብትና ጊዜ ደግሞ እርስ በእርሳቸው በደንብ እንዲተዋወቁና ልጆቻቸውን በጋራ እንዲያሳድጉ ረድቷቸዋል። ዘለግ ያለ የጎርብትና ቆይታቸው አንዳቸው የአንዳቸውን ስጋትና ስሜት እንዲወያዩና እንዲመከሩበት እድል ሰጥቷቸዋል።

ሁለቱም ወይዘሮዎች የቤት እመቤቶች ናቸው። ልጆቻቸውን እና የትዳር አጋሮቻቸውን ወደሥራና ትምህርት ቤት ከላኩ በኋላ ረጅሙን ሰዓታቸውን የቤታቸውን ሥራ እየሠሩ እንዲሁም እርስ በእርሳቸውም የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሱ ሲወያዩ የሚቆዩበት ጊዜ ነው።

በወጋቸውም መሃል ግን ሁለቱ ወላጆች የልጆቻቸው የትምህትርት ቤት ውሎና የትምህርት ሁኔታ እጅጉን ያሳሰባቸው ይመስላል። በየቀኑ የሚገናኙት ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም የተማሩ ቢሆንም ልጆቻቸውን በራሳቸው መንገድና በሚፈልጉት ሁኔታ ለማሳደግ በማሰብ ሥራቸውን ትተው የቤት እመቤት መሆንን ምርጫቸው ያደረጉ ናቸው። ታዲያ እነዚህ እናቶች በጠዋት ተነስተው ልጆቻቸውን አጥበው፣ አልብሰው አብልተውና አጠጥተው እንዲሁም ቀን ላይ የሚመገቡት ምግብ አስረው ወደ ትምህርት ቤት ይሸኟቸዋል። የማለዳ ሥራቸውን አከናውነው ልጆቻቸውን ከሸኙ በኋላ የቀረውን ጊዜ ሥራቸውን እየሠሩ በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮቻቸውን እያነሱ ሲጨዋወቱ ነው የሚውሉት።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም ከተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም ከመገናኛ ብዙሃን ያገኟቸውን ሃሳቦች ሰማሽ! ሰማሽ! ተባብለው ይጀምሩና ብዙ ያወሩበታል፤ የራሳቸውን ሃሳብ ይለዋወጡበታል፤ ይከራከሩበታል ቢሆን ብለው የሚያስቡትን የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጡበታል ስጋታቸውንም ሳይናገሩ አያልፉም።

ዛሬም እነዚህ እናቶች በእጅጉ ያሳሰባቸው የልጆቻቸው የትምህር ቤት ውሎና የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ነው። ሁለቱም ልጆቻቸውን በተለያዩ የግል ትምህርት ቤቶች ብዙ ዋጋን ከፍለው የሚያስተምሩ ነገ ላይ ዛሬ የከፈሉትን ዋጋ በእጥፍ እናገኛለን ብለው የሚተጉ እናቶች ናቸው። ታዲያ ዛሬ ላይ ስለ ግል ትምህርት ቤቶችና ስለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የሚሰሙት ሁሉ አጉል ሆነባቸውና ለውይይት አቀረቡት።

“ሰላም፣ እንዲያው መንግሥት ዛሬ ላይ እነዚህን ትምህርት ቤቶች በቃ ዝም አላቸው ማለት ነው?" ስትል የውይይት በሩን የከፈተችው ወይዘሮ አዜብ ናት። ተጠያቂዋ ሰላምም ፣ " ዝም ቢላቸው ነው እንጂ ክፍያ አትጨምሩ ሲላቸውና መጽሐፍ ራሴ አሳትማለሁ ሲል እነሱ የተለያዩ ምክንያቶችን እየፈጠሩ አንዴ ጉዞ ሌላ ጊዜ ሌላ እያወሩ ብር መሰብሰባቸውን አልተውም፤ እሱስ ይሁን ብንል እንኳን ልጆቻችንን ኢትዮጵያዊ መሆን ተሳናቸው እኮ " በማለት የወጨው ብዛት ግርም እንዳላት ትናገራለች።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም ከክፍያውም ከሁሉም ከሁሉም በላይ ያሳሰባቸው ልጆች በሚያገኙት ትምህርት ኢትዮጵያዊ ከመሆን ይልቅ ፈረንጅ እየሆኑ መምጣታቸው ነው። እሱስ ይሁን ግን ምናለበት ለሚያስተምሯቸው ልጆች ሥነ ምግባርም ያን ያህል ቢጨነቁ በማለትም ያክላሉ። የሥነ ምግባሩን ነገር ማንሳትም አያስፈልግም እያሉ የሚያወሩት ሁለቱ ወላጆች አንዳንዴ ልጆቻቸው የማያውቋቸው እንደሚሆኑና የሚጠቀሟቸው ቃላት ራሳቸው እንደሚያስደነግጣቸው ይወያያሉ።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም በውይይታቸው መካከል ስለ ኑሮ ውድነቱም ጣል ያደርጋሉ። በተለይም በዚህ ኑሮ ውድነት ልጆቻቸውን የተሻለ ነገር አብልተውና አጠጥተው ስለማደራቸው ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ በአንጻሩ ግን እንዲህ ዋጋ የሚከፈልባቸው ልጆች ነጋቸው አስከፊ መሆኑን ሲያስቡ ይጨነቃሉ።

እነዚህ እናቶች በዚህ ጉዳይ ላይ መንግሥት እጁን ያስገባ ብለውም መመኘታቸው አልቀረም፤ በተለይም በትምህርት ቤቶች ዙሪያ የሚከፈቱ መጠጥ ቤቶች፣ ጫትና ሲጋራ የሚሸጥባቸው ሱቆች፣ እንዲሁም ቪዲዮ ማሳያና ፕላይ ስቴሽን ማጫወቻ ቦታዎች ለልጆቹ መበለሻሸት ትልቅ ሚና እየተወጡ እንዳሉ በቁጭት ይወያያሉ፤ ነገር ግን መንግሥትም ሆነ ትምህርት ቤቶቹም እያዩ እንዳላየ የሚያልፏቸው ጉዳይ ግልጽ እንደማይሆንላቸው ይናገራሉ።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም በተለይም ትምህርት ቤቶች በሚጠሯቸው ስብሰባዎች ላይ እየተገኙ እነዚህ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ሳይሰጡ አላለፉም፤ ነገር ግን በአንድ እጅ ማጨብጨብ እየሆነባቸው መምጣቱም ልባቸውን ይነካዋል።

ዛሬማ መንግሥት በተለይም ለትምህርት ሥርዓቱ እየሰጠው ባለው ትኩረት እናቶቹ ያመሰግናሉ። አሁን ደግሞ በተለይም ወላጅ ከሌለው ላይ ልጁን የተሻለ ለማድረግ የሚያስተምርባቸው የግል ትምህርት ቤቶች ሊፈተሹ ደረጃም ሊወጣላቸው መሆኑን ወይዘሮ አዜብ ሲናገሩ፣ ወይዘሮ ሰላም ሃሳቡ ድንቅ መሆኑን ከመግለጻቸውም በላይ እጅግ ተደስተዋል።

ስማቸው ኢንተርናሽናል ተግባራቸው ግን ከእነርሱ የማይጠበቅ ብዙ ትምህርት ቤቶች መዲናዋን አጣበዋል ፤ ይህ መሰሉ ቁጥጥር እና ክትትል ግን ሁሉን ወደመስመር ለማስገባት ሚናው ትልቅ መሆኑንም ያምናሉ።

ወይዘሮ ሰላምና ወይዘሮ አዜብ ትምህርት ቤቶች የሚያስከፍሉትን ያህል አለማስተማራቸው በተለይም ደግሞ ለሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ያላቸው የወረደ አመለካከት አንስተው ይወቅሳሉ። በተለይም የወይዘሮ አዜብ ልጅ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት፤ ዛሬ ላይ እሷ እንግሊዘኛውን በምታቀላጥፈው ልክ አማርኛው እየገባት አለመሆኑን እናቷ ትታዘባለች። ልጅቷ በትምህርቷ ጎበዝ የምትባል ብትሆንም ለአማርኛ ቋንቋ ያላት አተያይ ዝቅተኛ መሆኑና ለቋንቋ ትኩረት አለመስጠቷ ግን ውጤቷ የሚጠበቀውን ያህል እንዳይሆን እንዳደረገውም እናት በቁጭት ታወራለች።

ወይዘሮ ሰላምና ወይዘሮ አዜብ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን በቅኝ ግዛት ሳንገዛ እንዲህ የባዕድ ቋንቋና የውጭ ሀገር አምላኪ መሆናችንን ሲያስተውሉ ስሜታዊ ያደርጋቸዋል። ሁለቱም ወላጆች “እንዲያው ልጆቻችንን በዚህን ያህል ደረጃ መሳባቸው ምንድነው ጉዱ?" ሲሉም ይጠይቃሉ። መለስ ብለው ግን ራሳቸውን በመውቀስ “አንደኛ ነገር እኛም ልጆቻችንን ለቴክኖሎጂ ሰጥተን ቁጭ ብለናል፤ ድሮው እኛ እንዳደግንበት አብሮ ማውራት፣ ጎረቤት ሄዶ መጫወት ከእኩዮቻቸው ጋር አፈር አቡክቶ መጫወት ትተዋል፤ ከእኛ የባሰ ደግሞ ትምህርት ቤት ሲሄዱ እንግሊዘኛ መናገራቸው እንጂ የሀገራቸውን ቋንቋ መናገራቸውም ሆነ መውደዳቸው እንደ ጥፋተኛና እንዳላዋቂ እያሳያቸው ነው፤ ታዲያ ልጆቹ ላይ መፍረድስ ተገቢ ነው!?” በማለት ይቆጫሉ።

እነ ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም ከዚሁ ውይይታቸው ሳይወጡ ለሁለቱም ጎረቤት የሆነችውን ወይዘሮ እየሩስን ያነሳሉ ፤ ወይዘሮ እየሩስ እንደእነሱ የልጆች እናት ብትሆንም የመንግሥት ሠራተኛ በመሆኗ ቤት አትውልም፤ እናም ልጆቿን የምታሳድገው በሞግዚት ነው። “አታያትም እንዴ እየሩስ ጎረቤታችንን! ልጆቿን ለሞግዚት ጥላ ነው ሥራዋ የምትሄደው፤ ልጆቹ ከቤት ካለመውጣታቸውም በላይ ብዙ ሰዓታቸውን የሚያሳልፉት ፊልም በማየትና የተለያዩ ጌሞችን በመጫወት ነው። በመሆኑም አፋቸውን በአረብኛና እንግሊዘኛ ፈቱ፤ ይህ ደግሞ ከቤተሰቡ ጋር ለመግባባት አስቸጋሪ ሆነ። እርሷስ አንዴ ለሞግዚት ጥላ ሄዳ ነው፤ እኛ ቤት ቁጭ ብለን እያሳደግን መቼ ከዚህ ችግር ወጣን? ልጆቻችን መቼ እኛን መሰሉ? መቼ ኢትዮጵያዊ ቋንቋዎቻችንን አስያዝን ?” በማለት ራሳቸውን ይወቅሳሉ።

**ልጆቻችንን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት አስተማርን እያልን ማንነታችንን ከነአንጡራ ሀብታችን እያጣን እኮ ነው**

አሁንም አልረፈደም የሚሉት ሁለቱ ጎረቤታሞች፤ በተለይም መንግሥት አሁን ላይ የጀመረውን የቁጥጥርና የክትትል ሥራ አጠናክሮ ከቀጠለ ችግሩን መፍታት እንደማይከብድ ብሎም ልጆቻችንን እኛን መስለው አድገው ለውጤት እንደሚበቁም ያላቸውን ተስፋ ይናገራሉ።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም፣ የዛሬው ጭውውታቸው የሁለቱም የልብ ትርታ የሆነው የልጆቻቸው የትምህርት ቤት ጉዳይ ነው። በመሆኑ ተመስጠዋል፤ “አንችዬ! እንዲያው ይህ ምዘና ግን ምናቸው ይሆን የሚመዝነው?” ብለው አንዳቸው ለአንዳቸው ጥያቄ ይሰነዝራሉ። ሁለቱም በአንድ ቃል በሚመስል ሁኔታ “መጀመሪያማ ሊታይ የሚገባው ልጆቻችንን ፈረንጅ ከማድረግ አውጥተው ኢትዮጵያዊ ማንነትን ማላበሱ ላይ ሊሆን ይገባል። ይህንን ከራሳቸው የትምህርት ዘመን ጋር አጣቅሰው ሲያወሩ “እኛ እኮ መጀመሪያ "ሀ ሁ ሂ......ብለን ነው ፊደል የቆጠርነው፤ ከዚያም ሀገራችን ምን ትመስላለች? የሚለውን ደግሞ በተረት፣ በመዝሙር ዘምረን አውቀን ነው የተሻገርነው፤ ይህንን ዓይነት የትምህርት አካሄድ በመሄዳችን ደግሞ የፈረንጁ ቋንቋም አላመለጠንም፤ በጊዜው እሱንም አውቀነዋል።” በማለት ድሮና ዘንድሮን እያገናኙ ይጫወታሉ። ዛሬስ? የተባለ እንደሆነ አፋቸውን የሚፈቱት እንደ ወይዘሮ እየሩስ ልጆች በእንግሊዘኛና አረብኛ ፊልሞች ነው፤ ለትምህርት ደረሱ ተብለው ትምህርት ስንልክ የሚቀበላቸው ያው ቤት የጀመሩት ነገር ነው፤ ከዚያማ በቃ! ማንነታቸውን ሳያውቁ እንዲሁ ባዕድ ናፋቂ ሆነው ልፉታችንን ገደል ሰደውት ይቀራሉ።

ወይዘሮ ሰላምና ወይዘሮ አዜብ አሁንም የሚናገሩት በስሜት ነው፤ “እኛ እኮ ከሁለት ያጣ ሆነናል። ሀገራችን ላይ ቁጭ ብለን ራሳችን በፈጠርነው ችግር የውጭ ሀገር ዜጎች እያመረትን ነው፤ ልጆቻችንን ኢንተርናሽናል ትምህርት ቤት አስተማርን እያልን ማንነታችንን ከነአንጡራ ሀብታችን እያጣን እኮ ነው። ታዲያ ይህ ምዘና እና ቁጥጥር ይሉት ነገር ይህንን ይቀርፍ ይሆን?” ብለውም ስጋታቸውን መካከል ላይ ጣል ማድረጋቸው አልቀረም።

ልጆቻችን ለእኛም ለሀገራቸውም ባህልና ወግ እንዲሁም ቋንቋ ደንታ ቢስ እየሆኑ እኮ ነው፤ እናማ መንግሥት እመዝናለሁ ካለ መጀመሪያ ትምህርት ቤቶቹ እውነት ኢትዮጵያዊ ናቸው ወይ? ተማሪዎቻቸውን አስተምረው ማድረግ የሚፈልጉት አሜሪካዊ ነው? ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት? መምህር? አልያም ፓይለት? ብቻ እነዚህ ሊታዩ ይገባሉ።” ካሉ በኋላ ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም እንዲያውም መንግሥት ከውሳኔው ወይም ወደምዘና ሥርዓቱ ከመግባቱ በፊት እኛን ወላጆችን ጠርቶ ሊያወያይ ይገባል የሚለውንም አቋማቸውን አንጸባረቁ።

ወይዘሮ አዜብና ወይዘሮ ሰላም ልጆቻችን የፈረንጅ አምላኪ ለመሆን ያበቃቸው የመማሪያ መጽሐፍ በተለይም በግል ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጀው በብቃት ምዘናው ላይ ትኩረት አግኝቶ ይታይ ይሆን እያሉ ያወራሉ፤ ለእነዚህ እናቶች መጽሐፉ ምንም ዓይነት ኢትዮጵያዊነት የማይታይበት፤ ተረቱ፣ ምሳሌው፣ ሥዕሉ ሳይቀር የውጭውን ዓለም ብቻ ትኩረት ማድረጉ ያሳዝናቸው ይመስላሉ። እንዲያው እኛ በመጽሐፍ ጽፈንና አትመን የምናስተዋውቀው የምንዘምርለት ጀግና ወይም ታዋቂ ሰው አጥተን ነው? እነ ላሊበላና አክሱም እንዲሁም ሌሎቹ ቅርስ ተብለው በትምህርት የመካተት አቅም ያላቸው ይሆን? ብለው ቁጭት ባንገበገበው አንደበት ያወራሉ።

በመሆኑም መንግሥት በሚያሳትሟቸው መጽሐፍት ላይ ያለውንም ሁኔታ ተከታትሎ መስመር ማስያዝ ካልቻለማ ምኑን ምዘና ሆነው!? ለመጥፋታችን ግንባር ቀደሙ ምክንያት እኮ እነሱ በሚያሳትሟቸው መጽሐፍት ላይ የሚጠቀሟቸው ምሳሌዎችም ሆነ የሚያሰፍሯቸው ምንባቦች አንድም ኢትዮጵያዊ ወዝና ቃናን ያልተላበሱ መሆናቸው ነው። እነዚህ ሁለት እናቶች በዚህ መልክ ልባቸው የቆሰለበትን ብሎም የልጆቻቸው መጻኢ እድል ጭልምልም ብሎ እየታያቸው የተቸገሩበትን ጉዳይ የሰሟቸውን የታዘቧቸውን በቤታቸውም እየተከናወነ ልጆቻቸውም ላይ እያዩት ካሉት ችግር በሙሉ አንስተው ሲወያዩ ሰዓቱ በጣም ሄደ። ልጆችም ከትምህርት ቤት ሲመለሱ የሚበሉት ያስፈልጋልና በቀረው ጊዜ ደግሞ እሱን ለመሰራራት ሊገቡ ሆነ። ነገር ግን ሁለቱም እናቶች የመንግሥትን ሃሳብ አድንቀውና ደግፈው የብቃት ምዘናው ላይ ግን ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ወላጆች ቢገኙ ብለው በመመኘት ወደቀጣዩ ሥራቸው ሄዱ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ማሽነሪ አምራቾችን፣ ፈላጊዎችንና አቅራቢዎችን ማስተሳሰርን ያለመው መድረክ

ኃይሉ ሣህለድንግል

መንግሥት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ውስጥ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማድረግ ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር መሥራቱን ቀጥሏል።ዘርፉ በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በፋይናንስ፣ በማምረቻ ቦታ አቅርቦት፣ በመሠረተ ልማት እና በመሳሰሉት ያሉበትን ችግሮች ለመፍታት ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ተሠርተው ውጤቶችም ተመዝግበዋል።

ዘርፉ ከኮቪድ ወረርሽኝ፣ ከሰሜን የኢትዮጵያ ጦርነትና ከእሱ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጫናዎች የተነሳ ከደረሰበት ጉዳት እንዲወጣና መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ በተለይ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄም እንዲሁ ብዙ ሰርቷል፤ በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም ማሳደግ፣ ከሥራ ውጭ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ መመለስ፣ ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ለውጥ ማምጣት፣... የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል።በንቅናቄው አሁንም ዘርፉን ይበልጥ የሚያጎለብቱ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ከሚያመርቱት መካከል ማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች ይጠቀሳሉ።ለእነዚህ አምራቾች ምርቶች ገበያ በማመቻቸት በኩል እየተሰራ ነው።ሰሞኑንም ማሽነሪ አምራች አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ተግዳሮቶችና መልካም እድሎች ላይ የመከረና የፌዴራልና ክልል ከፍተኛ አመራሮች፣ የማሽነሪ አምራቾች ማህበር አመራሮች፣ አምራቾችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት መድረክ ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ እንደተጠቆመው፤ ባለፉት ዓመታት የሀገሪቱን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመደገፍ በርካታ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል።በዚህም የተለያዩ ስኬቶች ቢመዘገቡም፣ ሀገራዊ የመልማት ፍላጎትን የሚያሟሉ ግን አይደሉም።በመሆኑም ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ታሳቢ ያደረጉና እውቀትና ተግባር ተኮር እንቅስቃሴዎችን ማድረግ በማስፈለጉ የተለያዩ ርብርቦች እየተደረጉ ይገኛሉ።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል የማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎች አቅዶችና ተግዳሮቶች በሚል ርእስ ከማሽነሪ አምራቾችና ባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄደውን ይህን መድረክ በዓይነቱ ልዩ ሲሉ ገልጸውታል።በመድረኩ የሚካሄደው ውይይት ትልቅ ተስፋ የተጣለበትና በዘርፉ ያሉትን ማነቆዎች ለመፍታት ዓይነተኛ ድርሻ እንደሚኖረውም አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት እሴት የተጨመረበት ምርት በማምረት ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ በማድረግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሽግግር ለማምጣት፣ እያደገ ለሚሄደው የሕዝብ ቁጥር የሥራ እድል ለመፍጠር ሰፊና ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሀገር ውስጥ ጥሬ እቃን በሰፊው በመጠቀም ግብርናን ጨምሮ ለኢንዱስትሪ ግብዓት፣ ለአምራቾች ሰፊ የገበያ እድል በመፍጠር ማሽነሪዎችንና መሳሪያዎችን አምርቶ በማቅረብ የማኑፋክቸሪንግና የግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለኢኮኖሚ እድገቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ እንደ ሀገር በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት እንዲመጣ ለማድረግ በመንግሥት ደረጃ ስትራቴጂዎች ፖሊሲዎች ተቀይሰው ወደ ሥራ ተግብቷል። የኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የገቢ ምርት መተካት፣ የቆዳ ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ ገብተዋል።የአቅም ግንባታ ስትራቴጂ፣ የኬሚካል ስትራቴጂ በቅርቡ ደግሞ የማሽነሪ ማምረት ስትራቴጂና የመሳሰሉትና ትስስር የመፍጠር ስትራቴጂዎች እንደ ሀገር ተዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል።

በአደረጃጀት በኩልም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኢንስቲትዩቶች፣ ከሥራና ክህሎት ጋር የተያያዙ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አደረጃጀቶች ለዚህ ዘርፍ ራእይና ግብ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱም ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ እንደጠቆሙት፤ በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ ትልልቅ ግቦች ተቀምጠዋል።በተለይ በልማቱ እቅዱ መጨረሻ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ እስከ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት፣ አምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎችም የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዷል።

የገቢ ምርትን ለመተካት እየተከናወነ ባለው ተግባር 30 በመቶ የነበረውን የገበያ ድርሻ ወደ 60 በመቶ እንዲሁም ከ50 በመቶ በታች ወርዶ የነበረውን የማምረት አቅም አጠቃቀም ወደ 85 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።አዳዲስ

**ባለፉት አምስት ዓመታት ከ32 ሺ በላይ ማሽነሪዎች ለአምራች ኢንተርፕራይዞች በሊዝ ፋይናንስ እንዲተላለፉ ተደርጓል። ከእነዚህ ማሽነሪዎች ውስጥ ከሀገር ውስጥ ማሽነሪ አምራቾች የተገዙት በጣም ጥቂት ናቸው። ስለዚህም ዋናው ምክንያት በማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችና በሊዝ ፋይናንስ ተቋማት መካከል ያለው ሰፊ የመረጃና ተቀናጅቶ የመሥራት ክፍተት ነው**

ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም በኩል ሰፋ ያሉ እቅዶች ተቀምጠው እየተሠራ ነው፡፡

ይህንን አቅድ ማሳካት እንዲሁም የሥራ እድል መፍጠር የሚቻለው ለዜጎች የማምረቻ መሳሪያዎችን በማምረት የመሥሪያ ቦታዎችን ማቅረብ፣ የፋይናንስና የግብዓት ማነቆዎችን መፍታት እንዲሁም በክህሎት በኩል ያሉትን ችግሮች ተደራሽ በሆነ መንገድ መፍታት ሲቻል ነው።

እነዚህ ነገሮች ከተስተካከሉ ሥራ አጥነት የኛ ችግር አይሆንም፤ ነገር ግን ፋይናንስ ሳንዘጋጅ የመሥሪያ ቦታ ሳናቀርብ በተለይ ደግሞ ማሽነሪ ሳናቀርብ የሥራ አጥነት ችግርን መፍታት አንችልም ሲሉ ያብራሩት ሚኒስትሩ፣ አንድ ማሽን ማቅረብ ቢያንስ ከአስር ላላነሱ ዜጎች በቀጥታ የሥራ አጥነት ችግሮቻቸውን ይፈታል ሲሉ አመልክተዋል። ይሄ ቀጥተኛ ፋይዳው መሆኑን ጠቅሰው፣ ምርቱን በመጓጓዝ፣ በመሸጥ በኩል የሥራ እድል የሚፈጠርላቸውን ሌሎች ዜጎች ሳይጨምር መሆኑን አስታውቀዋል።በተለይ ማሽን በማምረት ላይ አተኩረን በመሥራት ማሽኑን ስናቀርብ የምንፈጠረው የሥራ እድል ጤናማና ዘላቂነት ያለው ነው ሲሉም ተናግረዋል።በዚህ መልኩ የሚፈጠረው የሥራ እድል ለዜጎች ተስማሚና ምቹ እንደሆነም ነው ያመለከቱት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሰፊ የሥራ አጥነት ችግር ባለበት እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሀገር ሁሉንም ማሽኖች ከውጭ ማምጣት የሚሆን አይደለም።የማሽነሪ ችግርን በራስ አቅም ለመፍታት ጥረት ማድረግም ያስፈልጋል።እንደዚያ ከሆነ በየደረጃው ከትንሽ እስከ ትልቅ የማምረቻ መሳሪያዎችን በማቅረብ የሥራ አጥነት ችግሮችን መፍታት ይቻላል።

‹‹ከዚህ አኳያ በምን ሁኔታ ላይ ነው ያለነው ብንል የማሽን ማምረት አቅማችን እያደገ፣ ከኛ አልፎም አንዳንድ ምርቶችን ወደ ውጭ መላክ ጀምረናል›› ሲሉም ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል።ሚኒስትሩ ማሽኖቹ ሲታዩ እውን እዚህ ሀገር ውስጥ የተሰሩ ናቸው የሚል ጥያቄ ያስነሳሉ ብለዋል።የጥራት ደረጃቸው፣ ጥንካሬያቸው፣ የማምረት አቅማቸው ለሥራ ያላቸው ተስማሚነት እንደ ሀገር በዚህ ዘርፍ እየተፈጠረ ያለው አቅም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ያመላክታሉ ሲሉም አብራርተዋል።

ከዚህ አኳያም በጣም ተስፋ ሰጪ የሆኑ ከውጭ ስናስመጣቸው የነበሩ ማሽኖችንና የማምረቻ መሳሪያዎችን እዚህ ማምረት የምንችልበት አቅም እየተፈጠረ መሆኑን የሚያመላክቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች አሉ ሲሉም አስታውቀዋል። የመለዋወጫ እቃዎች በማምረት ረገድም እንዲሁ እጅግ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቅሰዋል።

ይህ ዘርፍ ባሉበት የገበያ ትስስር ማነቆዎች፣ የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮች ምክንያት በሚፈለገው ደረጃ እንዳላደገ አስታውቀው፣ ይህን ችግር በውይይት መፍታት ይኖርብናል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ በአንድ በኩል ሰፊ የገበያ ፍላጎት አለ፤ ማሽን እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉ ዜጎች ፣ ኩባንያዎች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለማሽን ገበያ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው የሚፈልጉ አምራቾችም አሉ።መንግሥትም ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያመጣ ለማድረግ ይፈልጋል፤ ዘርፉ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቱ /ጂዲፒ/ው አሁን ካለበት ሰባት በመቶ ወደ 17 በመቶ ለማሳደግ የግድ የማምረቻ ማሽኖችን እያመረቱ ለዜጎች ማቅረብና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ይፈልጋል።

በዚህ መድረክ ማነቆዎቹ ምንድናቸው? እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ? ከማን ምን ይጠበቃል? በሚሉት ላይ መነጋገር ያስፈልጋል ሲሉ አመልክተው፣ መድረኩም በአንድ በኩል ለአምራቾቹ ገበያ በማመቻቸት ትልቅ ሚና ይኖረዋል፤ በሌላ በኩል ማሽን እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉ እንደ ልማት ባንክና የመሳሰሉት ተቋማት ከማን ምን ሊያገኙ እንደሚችሉ መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይመቻቻል ብለዋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ እንደ ሚኒስቴሩና ኢንተርፕራይዞች ልማት ይህን ትስስር የመፍጠር ኃላፊነት አለብን ሲሉ ገልጸው፣ ይህ ሥራ በተናጠል የሚሠራ እንዳልሆነም ተናግረዋል።‹‹ምን ዓይነት የቅንጅት ሥራ ሰርተን ነው ማሽነሪዎቹ ጥራታቸውንና ደረጃቸውን ጠብቀው በተመጣጣኝ ዋጋ ለገዥዎቹ የሚቀርቡት የሚሉትን የቤት ሥራዎች ወስደን እንሠራለን›› ሲሉም አስታውቀዋል።

መድረኩ እነዚህን ግቦች የሚያሳካ እንደሚሆን አቶ መላኩ ጠቅሰው፣ መድረኩ እንደተጠናቀቀ ማን ከማን ምን ይገዛል የሚለውን አውቀን በዚያ መሠረት ዝግጅት የምናደርግበትም ይሆናል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ሚኒስትሩ አምራች ኢንዱስትሪው ያሉትን እምቅ አቅሞች አስመልክተው አብነቶችን ጠቅሰው ሲያብራሩ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማዳበሪያ ብቻ ሳይሆን የማዳበሪያ ጆንያም ከውጭ ይመጣ እንደነበር አስታውሰዋል። በቅርቡ የሀገር ውስጥ ጆንያ ማምረቻዎች ይህን መሥራት ይችላሉ አይችሉም በሚለው ላይ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን ገልጸው፣ በዚህም ሙሉ በሙሉ ጥራቱን የጠበቀ ጆንያ የሚያመርቱ ወደ ስድስት የሚደርሱ ኢንዱስትሪዎች መገኘታቸውንም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህም በአንድ ሳምንት ብቻ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች አራት ሚሊዮን ጆንያ እንዲያመርቱ ትእዛዝ ተሰጥቷል።በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት አቅጣጫና ከገንዘብ ሚኒስቴር በወረደው ትእዛዝ መሠረት የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት ከእነዚህ አምራቾች ጋር በቀጥታ ግብይት መፈጸም አለበት የሚል ግልጽ አቅጣጫ መቀመጡንም አስታውሰው፣ በዚህ መነሻነትም እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ከኢትዮጵያ የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል ብለዋል።

እንደሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ለኤሌክትሪክና ለመሳሰሉት የሚውሉ ስማርት ምሰሶዎችም/ፓሎች/ ከውጭ እንዲመጡ ይደረግ ነበር።ለዚህም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር አምስት ኩባንያዎች ምሰሶዎቹን ለማምረት ውል እየገቡ ናቸው።ኢንዱስትሪዎቹ ለጊዜው አንድ ሺ የሚሆኑ ምሰሶዎችን እንዲያመርቱ ትእዛዝ ተሰጥቷል።

ለቱሪስቶች የሚሆን ‹‹ሳፋሪ›› የሚባል ተሽከርካሪ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሚገዛው ከታንዛኒያና ኬንያ እንደነበር አስታውሰው፣ ‹‹እነኚህን ተሽከርካሪዎች እንድንሰራ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀማሪ ናችሁ አትችሉም ሳይሉን በሀገር ውስጥ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች ማበረታት የምንችለው ደፍረን ይህን ማድረግ ስንችል ነው ብለው አዳዲስ ተሽከርካሪዎችን ሰጥተውን ቀሪ አካላቸውን እዚህ ሰርተን ወደ ገበያ እንዲገቡ እያደረገን ነው›› ሲሉም አብራርተዋል።አያይዘውም የኤሌክትሪክ ገመዶችን በሀገር ውስጥ የማምረት ሥራም በስፋት እየተጀመረ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማሽነሪዎች እዚህ እየተመረቱ ወደ ጅቡቲና ሶማሌ እየተላኩ ናቸው ሲሉም ጠቅሰው፣ ስለዚህ ያልተጠቀምንባቸው እምቅ አቅሞች አሉ ሲሉ አስገንዝበዋል።ከዚህ አኳያ ለአነስተኛም ለመካከለኛም ኢንዱስትሪዎች የሚውሉ ማሽኖች በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም እንዳለ በተጨባጭ ማረጋገጥ ተችሏል፤ አሁን የሚፈጠሩ ትስስሮችም ይህን ይበልጥ የሚያጠናክሩ ናቸው ብለዋል።

ስለዚህ የመንግሥት አካላት ሁላችንም በየደረጃው ኃላፊነታችንን በተሟላ መልኩ እንወጣለን፤ አምራቾችና የሊዝ ፋይናንስ ተቋማትም በእያንዳንዱ ምርት ላይ ያሉትን የእናንተን ተፈላጊ መስፈርቶች/ ስፔስፊኬሽን/ በሚያሟላ መልኩ ምርቶቹ ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራ መሥራት አለባችሁ ሲሉም አስገንዝበዋል።

ይህ ካልሆነ ካለብን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተዳምሮ የማሽነሪና የመለዋወጫ ገበያና ፍላጎቱን ልናሟላ አንችልም።ይህም መድረክ እነዚህን ግቦች በሚያሳካ መልኩ የሚካሄድ ይሆናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር አለባቸው ንጉሴ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ የተነቃቃና ውጤታማነቱ በግልጽ የሚታይ አምራች የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመገንባት ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው።በዚህም እንቅስቃሴ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ15 ሺ በላይ አዳዲስ አምራች አነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች መፍጠር ተችሏል።ኢንተርፕራይዞቹም በልዩ ልዩ መልኩ ከ16 ቢሊዮን ብር በላይ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገዋል ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾች የመሥሪያ ቦታ ፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የገበያ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲሁም የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዲሟላላቸው ተደርጓል፡፡

መድረኩ የአምራቾች ኢንዱስትሪዎች ዋንኛ አቅም የሆነውን ማሽነሪና መለዋወጫ በራስ አቅም እያመረቱ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርንም ሆነ ፈጠራን ከሀገራዊ አቅም ጋር በማጣጣም ቁልፍ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆኑትን የማሽነሪ አምራቾችን ለማገዝ የሚያስችል ሀገራዊ አቅም መፍጠርን ያለመ ነው፡፡


ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ የማሽነሪ አምራቾች በዘመናት በዘርፉ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ሳያገኙ በመኖራቸው የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች በተናጠልና በግላቸው ለመፍታት ጥረት አድርገዋል፤ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን መፍጠር ከተቻለ በኋላ ደግሞ ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በመመቻቸት ላይ ይገኛል።በዚህም የማሽነሪ አምራቾች ተሰባስበው ራሳቸውን ከማደራጀት ባሻገር በልዩ ልዩ መድረኮች ላይ ራሳቸውንና ምርቶቻቸውን በማስተዋወቅ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጥረት እያደረጉ ናቸው።

በዚህም የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ለአምራች ኢንተርፕራይዞች የቴክኖሎጂ አቅም፣ ምርትና ምርታማነት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ከማሽነሪ አምራቾች ጋር ተቀራርቦ መሥራት ብቻ ሳይሆን ማሽነሪ አምራቾችን ከአምራች ኢንተርፕራይዞች እኩል መደገፍ ለዘርፉ ልማት ወሳኝ መሆኑ ታምኖበታል።

ባለፉት አምስት ዓመታት ከ32 ሺ በላይ ማሽነሪዎች ለአምራች ኢንተርፕራይዞች በሊዝ ፋይናንስ እንዲተላለፉ ተደርጓል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ ዶክተር አለባቸው፣ ከእነዚህ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ማሽነሪ አምራቾች የተገዙት ማሽኖች በጣም ጥቂት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።ለዚህም ዋናው ምክንያት በማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችና በሊዝ ፋይናንስ ተቋማት መካከል ያለው ሰፊ የመረጃና ተቀናጅቶ የመሥራት ክፍተት ነው ብለዋል።

ይህ አካሄድ ከውጭ የሚመጡ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካትና በሂደትም ሀገራዊ የማምረት አቅምን ለማገንባት እንደማያስችል ጠቅሰው፣ የውጭ ምንዛሬ አቅምንም የሚፈታተንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራውን እንደሚጎዳም አመልክተዋል።‹‹መድረኩ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በኢንተርፕራይዝ ልማት በጋራ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ታምርት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ማሽነሪዎችንም ታምርት፤ እኛም እንሸምት›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

# ስፖርት



# የግል የበላይነት የቴኳንዶ ውድድር በአዲስ አበባ ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

የአዲስ አበባ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን በመጪው ግንቦት ወር መጀመሪያ በሚያካሄደው ለሁሉም ክፍት የሆነ የግል የበላይነት የቴኳንዶ ውድድር ቅድመ ዝግጅት እያደረገ እንደሚገኝ አስታውቋል።በውድድሩ የሚያሸንፉ ተወዳዳሪዎች በየእድሜ ክልላቸው እና በሚወዳደሩበት የክብደት መጠን ሽልማት እንደተዘጋጀላቸው ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ውድድሩን በገንዘብ ለመደገፍ ከሳኦል ሁነት አዘጋጅ ጋር በመተባበር የውል ስምምነት እንደፈጸመና ድርጅቱ ውድድሩን እንዲሳለጥ እየተሠራ መሆኑ ተናግሯል።የ2016 ዓ.ም ለሁሉም ክፍት የሆነ የግል የበላይነትን የቴኳንዶ ውድድር ከግንቦት 3 እስከ 6 በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ይካሄዳል።

በውድድሩ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የተውጣጡ የወርልድ ቴኳንዶ ተወዳዳሪዎች እንዲሳተፉ እድል መመቻቸቱም ተገልጿል።በዚህም 1ሺ እና ከዛ በላይ የሆኑ ተወዳዳሪዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል።ለዚህም ከክልሎች ጋር በመናበብ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን፤ የውድድሩ ምዝገባ እስከ ሚያዝያ 19 ድረስ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረትእንደሚሆንም ተጠቅሷል።

በመድረኩ የሚሳተፉ ስፖርተኞች በዓለም አቀፉ የቴኳንዶ የክብደት ሕግ መሰረት የተሻለ ብቃት የሚታይበት ኪሎ ግራምና ካታጎሪ እንደተመረጠ ተጠቁሟል።ውድድሩ በሦስት አይነት ዘርፎች የሚካሄድ ሲሆን፤ እነዚህም ፋይት፣ ፑምሴ እና ሰበራ የተባሉ ናቸው።በ-46 ኪሎ ግራም ሴቶችና ወንዶች፣ በ-53 ኪሎ ግራም ሴቶች፣ በ- 54 ፣ -58፣ እና -68 ኪሎ ግራም ወንዶች የፋይት ውድድሮች የሚካዱ ይሆናል።በፋይት የሚያሸንፉና የወርቅ ሜዳሊያ የሚያጠልቁ ስፖርተኞች 20ሺ ብር ይሸለማሉ።የብር ሜዳሊያ የሚያመጡ



ከግንቦት 3-6 በሚካሄደው ውድድር ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ የወርልድ ቴካንዶ ስፖርተኞች ይሳተፉበታል፤

10 ሺ ብርና የነሐስ ሜዳሊያ የሚያሸንፉ ስፖርተኞች ደግሞ 5 ሺ ብር የሚሸለሙ ይሆናል።

የፑምሴ ውድድር በሴቶችና ወንዶች ነጠላ የሚካሄድ ሲሆን ከ12-14 ዓመት የዕድሜ ክልል እና ወጣት ሴቶች ይሳተፋሉ።በአዋቂዎች ከ18 ዓመት በላይ ሴቶችና ወንዶች፣ ከ12-14 ዓመት ዕድሜ እና ከ15-17 ዓመት ወጣቶች ይካተታሉ።አዋቂዎች ውድድር 10 ሺ ብር ሲሸለሙ ወጣቶች 5 ሺ እና ታዳጊዎች 3 ሺ ብር የሚሸለሙ ይሆናል።

በሰበራ ውድድር እንዲሁ በታዳጊዎች፣ ወጣቶች እና አዋቂዎች በሁለቱም ጾታ ውድድሮች የሚካሄዱ ሲሆን አንደኛ ለሚወጡት የ3 ሺ ብር ሽልማት ተዘጋጅቷል።በተጨማሪም በሁሉም የውድድር ዓይነቶች የሜዳሊያና የምስክር ወረቀት ሽልማትም ይበረከታል።በውድድሩ የተለያየ ችሎታ ለሚያስመለክቱ ስፖርተኞች ልዩ ሽልማት ለመስጠት ታስቧል።

የአዲስ አበባ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላውን ዋሲሁን፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተወዳዳሪ የስፖርቱን ስነ-ምግባር፣ ሕግና ደንብ የሚያከብር እና ለስፖርቱ ብቁ ከሆነ መወዳደር እንደሚችል አስረድተዋል።ለተወዳዳሪዎች የውድድር እድልን ከመፍጠር ባሻገር ከተማንና ሀገርን የሚወክል ስፖርተኛ ለይቶ ለማውጣት ጉልህ ሚናን የሚጫወት እንደሚሆን ገልጸዋል።በተጨማሪም ስፖርቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝና አቅም እንዲኖረው እና የራሱን ሀብት እንዲያመነጭ እገዛን ያደርጋል።

ከማርሻል አርት ስፖርቶች አንዱ የሆነው የወርልድ ቴኳንዶ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ መነቃቃት ቢያሳይም እንደሌሎች ስፖርቶች ባለማደጉ ይህ ውድድር የንቅናቄ መድረክ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።ከግልና ከመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት በሁሉም ክልል እና ክፍለ ከተማ ስፖርቱ እንዲስፋፋ ለመስራት የሚያስችልም ነው ተብሏል።

ውድድሩ የተሳካ እንዲሆን ፌዴሬሽኑ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገና ለተወዳደሪዎች ውድድር ከሚጀመርበትን ቀን ቀደም ብሎ ያስታወቀ መሆኑ ተመላክቷል። የአካል ብቃታቸውንና ስነ ልቦናቸውን ከመጠበቅ አንጻር ዝግጅት እንዲያደርጉና ከትራንስፖርት እና ማደርያም ጭምር የቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ ተጠቁማል።የትራንስፖርት ሁኔታን ለማመቻቸትም ስፖንሰሮችን የማፈላለግ ስራ የሚሰራ ሲሆን ውድድሩ ቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት እንዲኖረውም ይሰራል።

ፌዴሬሽኑ ከውድድሩ አዘጋጅ ጋር ለውድድሩ ማስኬጃ 700 ሺ ብር ተፈራርሞ ገቢ ማድረጉን የገለፁት አቶ ጥላውን፣ ፌዴሬሽኑ ውድድሮችን የማዘጋጀት ጫናን ለመቀነስና የውድድር ዕድልን ለማስፋት በክፍለ ከተማ ደረጃ ፌዴሬሽኖችን አቋቁሞ የራሳቸውን ውድድርና ስልጣና እንዲያዘጋጁ እድሎችን እንዳመቻቸ አስረድተዋል።

ውድድሩ ሀገር አቀፍና ሰፊ እንደመሆኑ ከብሔራዊ ፌዴሬሽን ጋር በማነጋገርና በመደጋገፍ ለስኬታማነቱ እየተሰራ ነው።የውድድሩን መክፈቻ ለማድመቅና ውድድሩ ብዙኀኑን ተደራሽ እንዲያደርግ ማህበራዊ ሚዲያን ጨምሮ፣ በብሮድካስትና በህትመት መገናኛ ብዙሀን ለማስተዋወቅም ታቅዷል።

ውድድሩ ወደፊት ለሚካሄዱት የክፍለ ከተሞች እና የክለቦች ውድድር እንደግብዓት የሚያገለግል ስለሆነም በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ ተገልጿል።